## ምዕራፍ አምስት።

# የያህዌ ምስክሮችና «የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን»።

የስሕተት ትምህርቶች በየዘመናቱ መልካቸውንና ስሞቻቸውን ይለዋውጣሉ እንጂ መሠረተ ሐሳባቸውና መንፈሳቸው ድሮ እንደነበረ አሁንም ያው ነው። በነቢያትና በሐዋርያት የሠራው እውነተኛው የእግዚአብሔር መንፈስ በየዘመናቱ በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል እየሠራ ይኖራል። እንደዚሁም የሐሰት መንፈስ በየዘመናቱ የሰዎችን ነፍሳት ለማጥመድ መጣሩ አይቀርም።

በዘመናችን ስለሥላሴ ማለት በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ መካከል ስላለው ግንኙነት በጥንትም ሆነ በዘመናችን አብያተ ክርስቲያናት ተቀባይነት የሌለውን ትምህርት ከሚያስተምሩ ውስጥ የያህዌ ምስክርችና ራሳቸውን «የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን» ብለው የሚጠሩ ናቸው። የእነዚህ አጀማመርና ትምህርታቸው እንዴት እንደሆነ ቀጥለን እናያለን።

## የያህዌ ምስክሮች ታሪክና አጀማመር።

የያህዌ ምስክርች ታሪካዊ አጀማመር ከመሥራቹ ከቻርለስ ራሰልና /1852 ዓ.ም - 1916 ዓ.ም/ ከተከሉት ሌሎች መሪዎች ሕይወት ጋር የተገናኘ ነው። ራስል በልጅነቱ ወላጆቹ የቤተ ክርስቲያን ሰዎች ቢሆኑም ከቤተ ክርስቲያን ወደ ቤተ ክርስቲያን እየቀየረ በ1870 ዮናስ ዌንዴል በሚባል ሰው በሚመራ የአድቬንቲስት ቡድን ውስጥ ገባ። እነዚህ ቡድኖች ክርስቶስ ቀደም ብሎ

በ1844 እንደታሰበው ዳግም ያልመጣው በአቆጣጠር ስሕተት ስለሆነ ከ1873-74 በእርግጥ ይመለሳል ብለው ያምኑ ነበር። ክርስቶስ በተባለው ጊዜ /በ1873-74 ዓ.ም/ ባልተመለሰ ጊዜ ራስል፥ ባርቡር ከሚባል አድቬንቲስት ጋር በመሆን ክርስቶስ በማይታይ ሁኔታ ወይም በመንፈሳዊ መንገድ ተመልሷአል ብሎ ማስተማር ጀመረ። በ1879 ዓ.ም ራሰል ከጓደኛው ከባርቡር በሌላ ክርክር የተነሣ ተለይቶ አዲስ መጽሔት ማሠራጨት ጀመረ። በ1879 ዓ.ም ራስል ከተማሪዎቹ አንዷን አገባ። ሚስቱ እስከተለያዩ 1897 ዓ.ም ድረስ የሥራው ብርቱ ደጋፊ ነበረች። ራሰል የሥራውን ወጪ፥ ከነበረው የወንዶች ልብስ ሱቅ ይሸፍን ነበረ። የያህዌ ምስክሮች በራሰል አማካይነት ዎች ታወር ማኅበር በሚል ስያሜ በይፋ የተቋቋሙት በታኅሣሥ ወር 1884 ዓ.ም ነበር።

ራሰል ለሁለት ጊዜያት ወደ ፍርድ ቤት ተወስዶ ተረትቷል። አንደኛው ከተለመደው አምስት እጅ ፈጥኖ የሚደርስ ስንዴ እንደሚሸጥ ባሠራጨው ዜና ምክንያት ተቃውሞ ተጽፎበት፣ ያለ አገባብ ስሜ ጠፍቷል በማለት በተቃዋሚው ላይ ክስ በመመሥረቱ ነበር። በተደረገው ምርምራ ራሰል ሲሸጥ የነበረው ስንዴ እንዲያውም ከተለመደው ስንዴ በጥራት ያነሰ እንደሆነ ለማረጋገጥ ተችሏል። ቀደም ብሎ ቄስ ሮስ የተባሉ ካናዳዊ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ራሰል የቤተ ክርስቲያን ምስክርነት ሳይሰጠው፣ በግብረገብም ሆነ በትምህርት በቂ ምስክርነት ሳያገኝ ራሱን በራሱ በመሾም የሚያስተምር ሰው ነው በማለት አንድ ጽሑፍ አውጥተው ነበር። በዚህ ጽሑፍ የተነሳ ራሰል ያለአገባብ ስሜን አጥፍተዋል በማለት ቄስ ሮስን ከሰሰ። ወደ ፍርድ ቤት በቀረቡ ጊዜ ራሰል የተባለው ነገር ሁሉ ውሸት ስለ መሆኑ ማስረጃ እንዲያቀርብ በተጠየቀ ጊዜ የመጽሐፍ ቅዱስ ቋንቋዎችን ማለት ዕብራይስጥንና ግሪክን ጠንቅቆ የሚያውቅ ሊቅ

ጀመሩ። ራዘርፎርድና ደጋፊዎቹ በ1931 ዓ.ም የይሆዋ ምስክሮች የሚል አዲስ ሲያሜ በመውሰድ ከተገነጠሉት ራሳቸውን ለዩ።

ራዘርፎርድ በጥር ወር 1942 ዓ.ም ሞተ። እርሱን የተካው ሦስተኛው የማኅበሩ ፕሬዝዳንት ናታን ሆሜር ኖር /1905-1977/ የተባለ ሰው ነበር። በኖር ዘመን በ1943 የዋች ታወር የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት የተባለው ተከፈተ። ብዙ መጻሕፍትም ታተሙ።

New World Translation የተባለው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉማቸው በ1961 ዓ.ም ታትሞ ወጣ። ከአርማጌዶን በኋላ የይሆዋ ምስክሮች የዓለምን መንግሥታት ይወርሳሉ የሚለው የኖር ልዩ ትምህርት ነበር። ኖር በ1977 ዓ.ም በሞተ ጊዜ ፍሬድሪክ ፍራንዝ አራተኛው መሪ ሆነ። ፍሬድሪክ ፍራንዝ የይሆዋ ምስክሮች ሚሲዮናዊ እንቅስቃሴ አበረታታ። በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ የመጽሔቶቻቸው ቅጂዎች እየታተሙ እንዲሰራጩ አደረገ። ፍሬድሪክ ፍራንዝ በታኅሣሥ ወር በ1992 ዓ.ም በሞተ ጊዜ ሚልተን ጆ ሄንሼል የሚባል ሰው መሪያቸው እንዲሆን መርጠው እስካሁን እየተንቀሳቀሱ ነው።

## ትምህርታቸው።

ከትምህርታቸው ተቀዳሚው ምሥጢረ ሥላሴን መካድ ነው። የይሆዋ ምስክሮች እውነተኛው አምላክ አንድ አካል ያለው ይሆዋ ብቻ ነው ይላሉ። ምንም እንኳን እግዚአብሔር «እኛ» እያለ የተናገረበትንና ኤሎሂም የሚለውን ብዛትን የሚያሳይ የእግዚአብሔር ስም መኖሩን ቢያውቁም፣ ሥላሴን ይክዳሉ። እንደእነርሱ ትርጓሜ «እኛን» የተጠቀመው እግዚአብሔር ግርማውን ለመግለጽ እንጂ በቁጥር ብዛት ስላለው አይደለም።

የያህዌ ምስክሮች ምንም ሌሎች ስሞች ቢኖሩም «ያህዌ» የእግዚአብሔር እውነተኛና ፍጹም ስም ነው ይላሉ።

የያህዌ ምስክሮች የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ፍጹም አምላክነት ይክዳሉ። እንደነርሱ አባባል ጌታችን ብዙ ችሎታ ቢኖረውም ሁሉን ቻይ፥ አይደለም። ኢየሱስ ክርስቶስ በያህዌ የተፈጠረ ነው። ክርስቶስ የያህዌ የመጀመሪያው ፍጥረት እንደመሆኑ ከዘላለም የነበረ ሳይሆን መጀመሪያ አለው ብለው ያስተምራሉ።

የያህዌ ምስክሮች የጌታችንን ፍጹም አምላክነትና የሥላሴ ሁለተኛው አካል መሆኑን ብቻ ሳይሆን የመንፈስ ቅዱስንም አምላክነት ይክዳሉ። መንፈስ ቅዱስ የራሱ አካል የሌለው የማይታይ የእግዚአብሔር ኃይል ብቻ ነው ይላሉ።

ለያህዌ ምስክሮች ከስም ሁሉ በላይ የያህዌ ስም ነው። የዓለም ታሪክ እንቅስቃሴና ግብ የያህዌን ስም ታላቅነትና ሥልጣን ማረጋገጥ ነው። እንደነርሱ አባባል የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት ዋና ዓላማ ሰዎችን ከኃጢአታቸው ለማዳን ሳይሆን የያህዌን ስም ታላቅነት ለማብሠርና የሚመጣውን የእግዚአብሔር መንግሥት ለማብሠር ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስን በሦስት ጊዜያት ከፍለው ያዩታል። እነርሱም ሰው ከመሆኑ በፊት፥ ሰው በሆነ ጊዜና፥ ሰው ከሆነ በኋላ ያለበት ሁኔታ ናቸው። ሰው ከመሆኑ በፊት ማለት ወልድ በእግዚአብሔር ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ ከማርያም እስከተወለደበት ጊዜ ድረስ ሎጎስ ወይም የእግዚአብሔር ቃል ነበረ ይላሉ። ይህ ማለት ግን ክርስቶስ ከእግዚአብሔር ጋር እኩል ነበረ ማለት አይደለም። ሎጎስ ወይም የእግዚአብሔር ቃል የነበረው ክርስቶስ ከእርሱ በኋላ ለተፈጠሩት ፍጥረታት የእግዚአብሔር አፍ /አፈ- ቀላጤ/ ነበረ። ወልድ ከሌሎች

ፍጥረታት ሁሉ የሚበልጥ የያህዌ ዋና ሠራተኛ /ባለሥልጣን/ ነው ለማለት ይቻላል።

ለያህዌ ምስክሮች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከምስቱ ጊዜያት በየትኛውም ቢሆን ከያህዌ ጋር እኩል የሆነበት የለም። እንዲያውም ሰው ከመሆኑ በፊት መልአክ ነበረ። ሰው ከመሆኑ በፊት በሰማይ የሚታወቀው እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ሳይሆን ሚካኤል ተብሎ ነው ይላሉ። በዚህ መሠረት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሌሎች መላእክት የሚለየው በደረጃ እንጂ በዓይነት አይደለም በዚህም መሠረት ጌታችን እንደ ማንኛውም መልአክ ፍጡር ነው ብለው ያምናሉ።

ምንም እንኳን ወልድ ሰው ከመሆኑ በፊት ፍጡር ቢሆንም ከአማልክት እንደ አንዱ እንደሆነ ይናገራሉ። ከዚህ የተነሣ New World Translation በተባለው በእነርሱ ትርጉም «ቃልም እግዚአብሔር ነበረ።» የሚለውን በእንግሊዘኛው God ብለው ሳይሆን በትንሹ ፊደል god ብለው ጽፈዋል። ይኸውም ፍጹም አምላክነቱን ለመካድ ያደረጉት ነው። ከዚህም የተነሣ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው በሆነ ጊዜ የነበረው ሁለት ባሕርያት ማለት ሰውም አምላክም ሳይሆን ሰው ብቻ ነው። በሰውነቱ ግን አዳም ከመውደቁ በፊት በገነት እንደነበረው ያለኃጢአት ነበረ። በገነት እንደነበረው አዳም ቢሆንም ፍጡር መሆኑ ነው።

ስለ ጌታችን መጨረሻ ሲናገሩ ያህዌ ክርስቶስን ከሞት ያስነሣው እንደ ሰው ልጅ ሳይሆን የማይሞት መንፈስ አድርጎ ነው። ከዚህ የተነሣ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን የሥጋ ትንሣኤ ይክዳሉ። ክርስቶስ ከሙታን የተነሣው ሰው ሆኖ በምድር ላይ በተመላለሰበት *ሥጋው ወይም* አካሉ ሳይሆን *«ሥጋ ያልሆነ የመንፈስ ልጅ»* ሆኖ ነው። ለዚሁም የሚሰጡት ምክንያት ክርስቶስ የአዳምን ኃጢአት ለመክፈል *ሥጋዊ* ሰውነትን መሥዋዕት አድርጎ ስለሰጠ ምንም የሚቀረው የለም የሚል ነው። ይኸንን

ትምህርታቸውን ለመደገፍ አብዛኛውን ጊዜ የሚጠቀሙት 1ጴጥ. 3፥18ን ነው። አንዳንዶችም ያህዌ የሙሴን ሥጋ እንደሰወረው የክርስቶስንም ሥጋ ሰውሮት ይሆናል ይላሉ።

አምላክነቱን ለመካድ ለማስረጃነት ከሚጠቀሟቸው ጥቅሶች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው። ዮሐ. 14፥28፦ «እኔ እሄዳለሁ ወደ እናንተም እመጣለሁ እንዳልኋችሁ ሰማችሁ። የምትወዱኝስ ብትሆኑ ከእኔ አብ ይበልጣልና ወደ አብ በመሄዴ ደስ ባላችሁ ነበር።»

በዚህ ጥቅስ ጌታችን «የምትወዱኝስ ብትሆኑ ከእኔ አብ ይበልጣልና» ሲል ቀደም ብለው የአርዮስ ተከታዮች፥ አሁን ደግሞ የያህዌ ምስክሮች እንደሚተረጉሙት፥ በሰውነቱና በባሕርይ ከአብ ማነሱን ሳይሆን፥ የምድር ላይ ተልእኮውን ማለት የሰዎችን ልጆች ደኅንነት ለመፈጸም በበጎ ፈቃዱ ራሱን ዝቅ አድርጎ ለአብ መታዘዙን በማመልከት ነው። ፊልጵ. 2፥5-11 ተመልከት። ስለዚህ ሐረጉ የክርስቶስን ምድራዊ ደረጃ፥ ትሕትናውንና ዝቅ ዝቅ ማለቱን፥ የባሪያውን መልክ ይዞ ራሱን ማዋረዱን፥ በማመልከት የተጻፈ ነው። እርሱ የማይታይ አምላክ ምሳሌና ገላጭ ነው። ዕብ. 1፥3። ቈላ. 1፥15። ወንጌላዊው ዮሐንስም «መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም! በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ተረከው» ይላል። ተራኪ ወይም ገላጭ መሆን በተለይም ውሱን ለሆነ ሰው በሚገባ መንገድ መግለጽ በገላጩ በኩል ራስን መወሰንን ያስከትላል። ይህ ራስን መወሰን በገላጩ በራሱ ምክንያትና ባሕርይ ሳይሆን ገለጣው በሚደረግለት ውሱን ሰው ምክንያት ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «አብ ከእኔ ይበልጣል» ብሎ የተናገረው ለሰው ብሎ ለራሱ የውሱንነት ጠባይ በመውሰድ የማይወሰነውና የማይታየው አምላክ ገላጭ በመሆኑ ነው። ጌታችን ይኸንን የገላጭነት ሥራ ባይወስድ

ኖር ግንም አምላክን ለማወቅ ባልቻለ ነበር። በዚህ መንፈስ ነው የአትናቴዎስ የእምነት መግለጫ ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ባሕርይ ሲናገር «በሰውነቱ ከአብ ያነሰ በመለኮቱ ከአብ ጋር የተካከለ» የሚለው። በዮሐንስ ወንጌል የተጠቀሱትንና ሌሎቹንም ጥቅሶች ማለት 5፥19፤ 7፥16፤ 10፥29 የምንረዳው በዚሁ ዓይነት ነው። የዘላለም የእግዚአብሔር ቃል በመሆኑ ከአብ ጋር እኩል ክብርና ስግደት የሚገባው የእግዚአብሔር ልጅ ነው። ምንም እንኳን ወልድ የገላጭነት ተልእኮውን ለመፈጸም ራሱን ዝቅ ማድረጉን ይህ ጥቅስ ቢናገርም ስለ ወልድ ፍጡርነት የሚናገረው የለም።

ራእይ 3፥14፦

> «በሎዶቅያም ወዳለው ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ፦ አሜን የሆነው፥ የታመነውና እውነተኛው ምስክር በእግዚአብሔርም ፍጥረት መጀመሪያ የነበረው እንዲህ ይላል»። በዚህ ጥቅስ ውስጥ «በእግዚአብሔርም ፍጥረት መጀመሪያ የነበረው» የሚለውን የእንግሊዘኛው ትርጉም RSV "the begining of God's Creation" ይላል»። NIV "the ruler of God's Creation" ይላል። NEB "the prime source of all God's Creation" ይላል። GNB "the origin of all that God has Created" ይላል። JB ደግሞ "the ultimate source of God's Creation ይላል።

ከዚህ ላይ የሚነሣው ጥያቄ አግርኛው እንደ RSV «የእግዚአብሔር ፍጥረት መጀመሪያ» ብሎ ክርስቶስን ሲጠራ ምን ማለቱ ነው የሚለው ነው። ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜዎች ግልጽ በሆነ መንገድ ገልጸውታል። NIV የተባለው ትርጉም የእግዚአብሔር ፍጥረት ገዥ /አዛዥ/ በሚል ይፈታዋል። GNB ደግሞ፦ የእግዚአብሔር ፍጥረት ሁሉ ምንጭ ብሎ ይፈታዋል።

NEB የእግዚአብሔር ፍጥረት ጥና ምንጭ ብሎ ይተረጉማል። «የእግዚአብሔር ፍጥረት ጥና ምንጭ» ብሎ ይፈታል። JB እንደገና «የእግዚአብሔር ፍጥረት ጥና ጥንጭ ብሎ ይተረጉማል። «የእግዚአብሔር ፍጥረት መጀመሪያ» የሚለው የግሪኩ ሐረግ የእግዚአብሔር ፍጥረት ምንጭ ወይም ገዥ የሚል ትርጉም ያለው እንደሆነ እናያለን። የያህዌ ምስክሮች ግን «በእግዚአብሔር ከተፈጠረው ፍጥረት የመጀመሪያው» ብለው ይተረጉሙታል። እግዚአብሔር ያለማንም እርዳታ ለብቻው በመጀመሪያ የፈጠረው ክርስቶስን ነው ይላሉ። ይህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አሻሚ የሆነ፣ በሁለት ዓይነት መንገድ ሊተረጐም የሚችል ሐረግ ሆኖ ከታየን በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ በግልጽ ከተጻፉ ከሌሎች ክፍሎች ጋር አመሳክረን ማየት ይገባናል።

ቀደም ብለን እንዳየነው ዮሐ. 1፥3 «ሁሉ በእርሱ ሆነ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም» ይላል። ያለ እርሱ የሆነ ከሌለ እርሱ ፈጣሪ እንጂ ፍጡር አይደለም። ደግሞም መጽሐፍ ቅዱስ «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ» /ዘፍ. 1፥1/ ይላል። እግዚአብሔር በመጀመሪያ ክርስቶስን /ኢየሱስን/ ፈጥሮ በእርሱ በኩል ሰማይንና ምድርን ፈጠረ አይልም። ክርስቶስ የመጀመሪያ ፍጡር ከሆነ ሰማይንና ምድር የመጀመሪያ ፍጥረት መሆናቸው ቀርቶ ሁለተኛ ወይም ሦስተኛ ፍጥረት መሆናቸው ነው። ይህ ግን ግልጽ የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል የሚቃረን ስለሆነ «የእግዚአብሔር ፍጥረት መጀመሪያ» ተብሎ በራእይ የተጻፈውን የእግዚአብሔር ፍጥረት ምንጭ ወይም ገዥ በሚል ትርጓሜው እንረዳለን።

ምሳሌ 8፥22

ስለጥበብ ሲናገር፥ «እግዚአብሔር የመንገዱ መጀመሪያ አደረገኝ ከቀድሞ ሥራዎቹ መጀመሪያ» ይላል።

የዚህን ጥቅስ ትርጉም በደንብ መረዳት የምንችለው ተከታዮቹን ጥቅሶች ተመልክተን አገባቡን ስንረዳ ነው። በምሳሌ 8፥22-36 የሚናገረው ጥበብ ነው። «የመንገዱ መጀመሪያ አደረገኝ ከቀደመው ሥራው መጀመሪያ» ብሎ የተናገረው ጥበብ በተከታይ ጥቅሶች «ከጥንቱ ከዘለላም ጀምሮ ተሾምሁ፥ ምድር ከመፈጠርዋ አስቀድሞ» ይላል። ይህ ብቻ ሳይበቃው በቍ.24 «ቀላያት ገና ሳይኖሩ እኔ ተወለድሁ... ከኮረብቶች በፊት እኔ ተወለድሁ» ይላል። ስለዚህ እኛ «እግዚአብሔር የመንገዱ መጀመሪያ አደረገኝ» የሚለውን በተከታዮቹ ጥቅሶች ግለት «ተወለድሁ» «ከጥንቱ ከዘላለም ጀምሮ ተሾምሁ» በሚል መንፈስ እንረዳለን እንጂ ተፈጠርሁ በሚለው መንፈስ አንረዳም። ከላይ እንዳየነው «እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰማይንና ምድርን ፈጠረ» ዘፍ. 1፥1። ከዚህ የምናየው ጥበብ እግዚአብሔር የመጀመሪያውን ፍጥረት «ሰማይንና ምድርን» በፈጠረ ጊዜ አብሮት እንደነበረ እንጂ ራሱ ፍጡር እንደሆነ አይደለም። የእግዚአብሔር ጥበብ የተባለው ክርስቶስ የመጀመሪያውን ፍጥረት «ሰማይንና ምድርን» ከእግዚአብሔር ጋር ሆኖ የፈጠረ ነበር እንጂ ፍጡር አይደለም።

ቈላስይስ 1፥15።

የያህዌ ምስክሮች በዚህ ክፍል «እርሱ ከፍጥረት ሁሉ በኩር ነው» የሚለውን እንደ ልማዳቸው ከፍጥረት ውስጥ የመጀመሪያው ነው ብለው ይተረጉማሉ። ክፍሉ ግልጽ እንዲሆንልን፦ ቈላ. 1፥15-17 እንዲህ ይላል፦ «እርሱም የማይታይ አምላክ ምሳሌ ነው፤ የሚታዩትና የማይታዩትም

ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ጌትነት ወይም አለቅነት ወይም ሥልጣናት በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኲር ነው ሁሉ በእርሱና ለእርሱ ተፈጥሮአል እርሱም ከሁሉ በፊት ነው ሁሉም በእርሱ ተጋጥሞአል።» «ከፍጥረት ሁሉ በኲር ነው» ሲል ከፍጥረት ቀዳሚ ነው ወይም ከፍጥረት በፊት ነበር ማለቱ ነው እንጂ ክርስቶስ የመጀመሪያው ፍጡር ነው ማለቱ አይደለም። ለዚሁም ማስረጃ የሚሆነን «የሚታዩትንና የማይታዩትን በሰማይና በምድር ያሉትን ሁሉን» መፍጠሩ ነው። ሁሉን ከፈጠረ እርሱ ፈጣሪ እንጂ ፍጡር አይደለም። ይኸንን ዮሐንስ በወንጌሉ «ሁሉ በእርሱ ሆነ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም /1፥3/ ብሎ ስለ ቃል ከጻፈው ጋር በአንድነት ካየን ፍጡር ከሚባል ማንኛውም ያለክርስቶስ የተፈጠረ እንደሌለ እናያለን። ፈጣሪ ስለሆነም ምላስ ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ ሊመሰክርና ጉልበት ሁሉ እንዲንበረከክለት ተገባው።

## «የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን»።

ራሳቸውን «የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን» ብለው የሚጠሩት በ1914 ዓ.ም እንደ ኤውሮጳ አቆጣጠር Assemblies of God ተብሎ ከሚታወቀው ከአሜሪካ የጴንጤቆስጤ እንቅስቃሴ ተገንጥለው የወጡ ናቸው። የተገነጠሉበትም ምክንያት ከጥንት ቤክርስቲያን ጀምሮ የነበረውን በኒቂያ የሃይማኖት መግለጫ ላይ የተመሠረተውን የሥላሴን ትምህርት በመቃወማቸው፥ ስለኢየሱስ ስም ባላቸው አመለካከትና፣ በጌታ ኢየሱስ ስም ዳግም ጥምቀት መፈጸም አለበት በሚል አቋማቸው ምክንያት ነበር። ከዚህ የተነሣ ከAssemblies of God

ስለተወገዱ በ1917 ዓ.ም በድርጅት መልክ ተደራጁ። በመጀመሪያዎቹ ዓመታት "New Issue" «አዲስ ነገር» ወይም "Jesus Only" /ኢየሱስ ብቻ/ እንቅስቃሴ በሚል ስያሜ ይታወቁ ነበር። ከ1930 ጀምሮ ግን «ኢየሱስ ስም» ጴንጤቆስጤ፤ ሐዋርያዊ "Apostolic" ወይም "Oneness" የዋሀድ /አንድ/ ጴንጠቆስጤ በሚል ስያሜ መታወቅ ጀመሩ።

## አጀማመራቸው።

በሚያዝያ ወር /1913 ዓ.ም በአሜሪካ ውስጥ ከሎሳንጀሊስ ከተማ ውጭ በተደረገው የዓለም አቀፍ የጴንጤቆስጤ ስብሰባ ላይ ሬ.ኢ. ማክአሊስተር የተባለ ካናዳዊ፣ ሐዋርያት በሥላሴ ስም /ማቴ. 28፥19/ ሳይሆን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አጠመቁ ብሎ አስተማረ። /የሐዋ. 2፥38/

ይኸንን ትምህርት የሰማ ፍራንክ ጂ ኤዋርት የተባለ አንድ የአውስትራሊያ ተወላጅ በዓመቱ በሚያዝያ 1914 ዓ.ም ገሌን ኩክ ከሚባል ጓደኛው ጋር ሆኖ በይፋ በገንዳ ውኃ በኢየሱስ ስም ተጠመቀ። ከጓደኛው ጋር እርስ በርስ ከተጠመቁ በኋላ ኤዋርትና ኩክ በስብከትና በመጽሔታቸው አማካይነት ትምህርታቸውን ማሠራጨት ጀመሩ። በትምህርታቸውና በስብከታቸው አንዳንድ መሪዎችንና አገልጋዮችን ማረኩ። ከዚህ የተነሣ በ Assemblies of God የጴንጤቆስጤ እንቅስቃሴ ክፍፍልና ብጥብጥ ተነሣ። በኢየሱስ ስም ዳግም የማጥመቁንና የሥላሴን ጥያቄ መርምሮ ከእልባት ለመድረስ ማኅበሩ በጥቅምት ወር 1915 ዓ.ም አንድ ጉባኤ ጠራ። ለሁለተኛ ጊዜ በ1916 ዓ.ም ሌላ ጉባኤ ጠርቶ «መሠረታዊ እምነቶች» በሚል ስያሜ አሥራ ሰባት አንቀጾችን የያዘ መግለጫ አወጣ። በዚህ መግለጫ ከጥንት ቤተ ክርስቲያን የተወረሰውን በኒቂያ የሃይማኖት

መገለጫ ላይ የተመሠረተውን የሥላሴ ትምህርት አጸደቁ። የAssemblies of God ማኅበር ከነበራቸው 585 አገልጋዮች ውሳኔያቸውን ያልተቀበሉትን 156 አሰወገዱ።

ከዚሀ ቀጥሎ ባሉት 30 ዓመታት በኢየሱስ ስም ብቻ መጠመቅ አለብን የሚሉት በተለያዩ መሪዎቻቸው እርስ በርስ ተከፋፍለው ትምህርታቸውን ማስተማር ጀመሩ። በእነዚያ ዓመታት ብዙዎቹ አንድ ለመሆን ያደረጉት ጥረት አልተሳካም። እርስ በርስ ካለያያቸው ውስጥ ገሚሶቹ በኢየሱስ ስም መጠመቅና በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ የአዲስ ልደት ምልክት ነው ሲሉ፥ ሌሎቹ ደግሞ አዲስ ልደትን በኢየሱስ ስም ከመጠመቅ ጋር ለማገናኘት አለመፍቀዳቸው ነበር። በ1945 ዓ.ም United Pentecostal Church በሚል ስያሜ አንድ ኅብረት ለመፍጠር በቁ። በ1971 ዓ.ም በዓለም ውስጥ ያሉት «በኢየሱስ ስም ብቻ» መጠመቅን የሚያምኑት ለማስተባበርና ሥራቸውን ለማቀናጀት Apostolic World Christian Fellowship የሚባል ድርጅት አቋቋሙ።

የትምህርታቸው ይዘት።

ሀ. እንደ አይሁድ ሃይማኖት እግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ አንድ ነው ብለው ያምናሉ። አንዱ እግዚአብሔር ራሱን በመገናኛው ድንኳን፥ በቤተ መቅደስ፥ በተለይም በስሙ እየገለጸ ኑርአል። ከዚሀ በመነሣት «ኢየሱስ» የተባለው ስም እግዚአብሔር ራሱን ሙሉ በሙሉ የገለጸበት የመለኮት ስም ነው ይላሉ። አንድ አማኝ በውኃ ጥምቀት የኢየሱስን ስም ጠርቶ ሲጠመቅ ከሞት ከተነሣው ጌታ ጋር ኅብረትን ይፈጥራል። ከተጠመቀም በኋላ የኢየሱስ ስም ስሙን በተሸከመው ላይ /የእግዚአብሔር መንግሥት

ምልክቶች እየታዩበት/ የኃይል ምንጭ ይሆንለታል ይላሉ።

ለ. የትምህርታቸው ዋና ይዘት እግዚአብሔር ራሱን ከብሉይ ኪዳን ጀምሮ በስሙ አማካይነት ገልጾአል የሚል ነው። ስሙ ሰው መለኮትን የሚጠራበት መንገድ ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር ራሱን ጠባዩን /በሕርዩን/ የሚገልጽበት እንዲሁም ሰው እግዚአብሔርን የሚገናኝበት መንገድ ነው። በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር የተጠራባቸው ብዙ ስሞች ቢኖሩም «ያህዌ» የተባለው መጠሪያው ራሱን የገለጸበት ነው ይላሉ። ይህም ስም ብዙ ቍጥር ሳይሆን ነጠላ ስለሆነ እግዚአብሔር በባሕርዩ ፍጹም አንድ መሆኑን ያሳያል ይላሉ። በተጨማሪም የእግዚአብሔርን አንድነት የሚገልጹ እንደ ዘዳግም 6፥4 የመሳሰሉ ጥቅሶችን ይጠቅሳሉ።

## ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ።

1ኛ. እግዚአብሔር የሚታይና የማይታይ ክሥተት አለው። በዚህ ምክንያት የወዲህኛው ዓለምና የወዲያኛው ዓለም ገጽታ አለው ማለት ነው። በአዲስ ኪዳን የወዲያኛው ዓለም ወይም የማይታይ ገጽታው በመንፈስ በኩል ሲገለጽ የወዲህኛው ዓለም ገጽታው በቃል በኩል ተገልጾአል። እንደዚሁም አብ የማይታየውን የእግዚአብሔር ገጽታ ሲያሳይ ወልድ ደግሞ የሚታየውን ክሥተት ይገልጻል። የእግዚአብሔር አንድነት በወዲያኛው ገጽታው የተጠበቀ ሲሆን በሚታየው ገጽታው ግን የሦስትነት ክሥተት አለው። በዚህ አገላለጻቸው በእግዚአብሔር ሦስትነት ማለት በሥላሴ ከሚያምኑት የሚለዩት ሦስትነቱን በዚህኛው ዓለም ክሥተት ብቻ

በመወሰናቸውና ዘላለማዊ ሦስትነቱን ባለማመናቸው ነው።

2ኛ. የእግዚአብሔርን አካል በዚህኛው ዓለም ማለት «በኢየሱስ» ሰብአዊነት ሲወስኑ መንፈስ ደግሞ እግዚአብሔር በወዲያኛው ዓለም ያለውን ህልውና የሚገልጽ ነው ይላሉ። «አካል» የሚለው ቃል ጥልቅና የተለያዩ ትርጉሞች እንዳሉት በመዘንጋት፥ አካልን በግዙፍነት ብቻ ከመረዳታቸው የተነሣ፥ በሥላሴ የሚያምኑት ሦስት እግዚአብሔሮችን እንደሚያምኑ አድርገው ይቆጥራሉ። እግዚአብሔር መንፈስ በመሆኑ መገለጹ አካል የሌለው ነው ለማለት አይቻልም። /ቀደም ብሎ ስለአካል የተሰጠውን ገለጻ ተመልከት/ እንደእነርሱ ትምህርት ሥጋ ለብሶ ሰው የሆነው የሥላሴ ሁለተኛው አካል ሳይሆን እግዚአብሔር በወዲያኛው ዓለም ራሱን የገለጸበት መንፈስ ነው።

3ኛ. በ1ጢሞ. 3፥16 «በሥጋ የተገለጠ» የሚለው ቃል የእግዚአብሔር ሦስትነት ከመገለጡ ወዲህ እንጂ ከዚያ በፊት እንዳልነበረ ያሳያል ይላሉ። /ነገር ግን ጌታችን በዮሐ 17· የጸለየውን ጸሎት ተመልከት/። በሥላሴ የሚያምኑት በሦስት በተለያዩ እግዚአብሔሮች እንደሚያምኑ አድርገው በስሕተት በመተርጎም ቈላስይስ 2፥9 «በእርሱ የመለኮት ሙላት ሁሉ በሰውነት ተገልጦ ይኖራልና» የሚለውን ይጠቅሳሉ። እኛ በሥላሴ የምናምነው «የመለኮት ሙላት ሁሉ» በጌታችን ሰውነት እንደ ተገለጠ እናምናለን። በዚህም ምክንያት ነው «እኔን ያየ አብን አየ» /«እኔና አብ አንድ ነን» ያለው። ዮሐ.14፥9። ቀጥሉ

ሲያብራራ ግን «እኔ በአብ እንዳለሁ፥ አብም በእኔ እንዳለ አታምንምን?» የሚል ጥያቄ አቅርቦ እናገኛለን። አብ በእኔ፥ እኔ በአብ የሚለው መተሳሰርን፥ አንድ ላይ መገኘትን ያሳያል እንጂ እኔ አብ ነኝ፥ አብም እኔን ነው የሚለውን ትርጉም አያሰጥም። በአብና በወልድ መካከል የ«አካል» ልዩነት ባይኖር ኖሮ «እኔ በአብ ...አብም በእኔ» ብሎ ለመናገር ባልተቻለ ነበር። እኔን ያየ አብን አየ ማለቱም በእርሱና በአብ መካከል ፍጹም የባሕርይ አንድነት መኖሩን ለማመልከት እንጂ «የአካል» ልዩነት መኖሩን ለመካድ ወይም ለማስቀረት አይደለም።

የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን መምህራን /ተከታዮች/ እግዚአብሔር በብዙ ቊጥር የተናገራቸውን ጥቅሶች ዘፍ. 1፥26፤ 3፥22 በተለያየ መንገድ ይተረጉማሉ። ጉርደን ማጂ የተባለው ደራሲ እግዚአብሔር ለመላእክት እንደሚናገር አድርጎ ሲተረጉም /የተከለ ማርያም ገዛኸኝን ተመሳሳይ ትርጓሜ «ኢየሱስን ግን ይሉታል?» በሚለው መጽሐፉ ከገጽ 12-17 ተመልከት።/ ዮሐንስ ፓተርሰን የተባለው ደራሲ ደግሞ ቃል ሥጋ ከመሆኑ በፊት የተለየ ነበር የሚል አቋም ስላለው እግዚአብሔር ከቃል ጋር እየተነጋገረ ነበር ብሎ ይተረጉማል። Dictionary of Pentecostal and Charismatic Movements ገጽ/649/።

ትምህርታቸው ከሰባልዮሳውያን የሚለይበት ነጥብ ቢኖር ሰባልዮሳውያን አንዱ አምላክ መጀመሪያ እንደ አብ ቀጥሎ እንደ ወልድ፥ ከዚያም እንደ መንፈስ ቅዱስ የተለያዩ ስሞችንና ገጽታዎችን በመውሰድ ተገለጸ ሲሉ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ተከታዮች በአንዱ አካል ምስቱም እንደሚገለጹ ይናገራሉ። ይህም ማለት የተለያየ አጠራር እንጂ አንድ አካል ብቻ ነው ማለት ነው።

## የኢየሱስ ስም።

ስለ ኢየሱስ ስም ያላቸው አመለካከት የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያንን ከሌሎች ልዩ ከሚያደርጋቸው ነገሮች ውስጥ ዋናው ነው። ምንም እንኳን በቃሉ አመጣጥ «ኢየሱስ» የተባለው ስም «ያህዌ ረዳ አዳኝ» የተባለውን ትርጉም የያዘ ቢሆንም ለዚህ ዘመን የእግዚአብሔር የተጸውዖ ወይም የግል ስም የኢየሱስ ስም ብቻ ነው ይላሉ። ይህ ስም የኢየሱስን ማንነትና የዓለም አዳኝ የመሆን ሥራውን ይገልጻል።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ተብሎ በሚጠራበት ጊዜም «ጌታና» «ክርስቶስ» ገላጭ ማዕረጋት ሲሆኑ «ኢየሱስ» ግን የተገለጠ ስም ነው። ኢየሱስ የተባለው ስም ሰብአዊነቱን ሳይሆን መለኮቱን የያዘ ነው። በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ለተወሰኑ ጊዜያት በአንዳንድ ሥፍራዎች ማደሩን መሠረት በማድረግና፥ በተለይም ቆላ. 2፥9 «በእርሱ የመለኮት ሙላት ሁሉ በሰውነቱ ተገልጦ ይኖራልና» የሚለውን በመጥቀስ እግዚአብሔር በአሁኑ ጊዜ የኢየሱስ ሰውነት ማደሪያው ሆኖ ዘወትር ይኖራል ይላሉ። ይህም በእግዚአብሔር አንድ የማይከፋፈል መንፈስና አንድ ሰብአዊ አካል አለ ከሚለው መሠረታዊ እምነታቸው ጋር የሚስማማ ነው። ስለዚህ አብ፥ ወልድ ተብሎ ሲነገር፥ መለኮታዊ መንፈስ የሆነ አብ፥ ሰው በሆነ በልጁ ማደሩ ነው ይላሉ። ስለዚህ ኢየሱስ በመለኮቱ አብ ነው በሰብአዊነቱ ደግሞ ወልድ ነው። መንፈስ የሆነው አብ ሥጋ ከመልበሱም በኋላ የማይወሰን ሆኖ ይቀጥላል።

የክርስቶስን ዘላለማዊነት ለየት ባለ መንገድ ይገልጻሉ። በመጀመሪያ አንድ አካል ወይም መንፈስ በሆነው በእግዚአብሔር ሐሳብ ወይም በዘላለማዊ እቅዱ ብቻ ነበር።

በሁለተኛ ደረጃ በዝምታ ከነበረው ከእግዚአብሔር ሐሳብ የመፍጠርና የማዳን ሥራው በተጀመረ ጊዜ እንደ «ቃል» ገለጸው። ስለዚህ «መንፈስ» እግዚአብሔርን በዘላለማዊነቱ ሲገልጽ «ቃል» ደግሞ እግዚአብሔር ከሌሎች ጋር በሚያደርገው ግንኙነት በጊዜ ሲገለጽ ነው ይላሉ። በቃልና በእግዚአብሔር መካከል የአካል ልዩነት መኖሩን ሳያምኑ በአንድ በኩል ቃል ከእግዚአብሔር የወጣ ነው ሲሉ በሌላ በኩል ደግሞ ቃል እግዚአብሔር ራሱ ነው ይላሉ።

በመንፈስነቱ እግዚአብሔር መለያየት ወይም ቅርጽ የሌለው ነው። ቅርጽ ወይም መልክ በሚይዝበት ጊዜ በሙሉ ባሕርዩ ይገኛል። ዞር ዞር የክርስቶስ አምላክነት በሰብአዊነቱ ውስጥ የገባው የዘላለም መንፈስ ወይም አብ ነው። አንዳንዶች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «አምላኬ አምላኬ ለምን ተውከኝ» ብሉ በመስቀል ላይ የጮኸውን ሲተረጉሙ መንፈስ የሆነው እግዚአብሔር ስለተለየው ነው ይላሉ። መንፈስ የሆነው እግዚአብሔር እንደገና ከሥጋው ጋር የተገናኘው ከትንሣኤ በኋላ ነው።

አንዳንዶች ደግሞ በአምላክነቱና በሰብአዊነቱ /በልጅነቱ/ መካከል ያለው አንድነት ጊዜያዊ እንደሆነና በመጨረሻም ሰብአዊነቱ ወይም ልጅነቱ እንደሚቀር ይናገራሉ። የማስታረቅ አገልግሎትን በምድር ላይ በመፈጸሙ ከፍጥረት በፊት መለያየት የሌለው፥ መንፈስ የሆነ አንድ አካል ያለው እግዚአብሔር እንዳለ እንደሚያስተምሩ ከፍ ብለን አይተናል። ከዚህ የተነሣ ለእነርሱ በክርስቶስ ዘላቂነት ያለው፤ የክብር አምላክ መሆኑ እንጂ ሰብአዊነቱና ልጅነቱ አይደለም። በሥላሴ የምናምን በአብና በልጅ መካከል ያለው ግንኙነት ዘላለማዊ እንደሆነ ስናስተምር እነርሱ ግን በሁለቱ መካከል ያለው ግንኙነት ተግባራዊ (ለመገለጥ) እንደሆንና

አንዳንዴም ጊዜያዊ እንደሆነ ይናገራሉ። ይህም አንድ «አካል» ከሚለው ትምህርታቸው ጋር የሚሄድ ነው።

## «የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን» በኢትዮጵያ።

በኢትዮጵያ የዚህ እምነት ተከታዮች አጀማመር የአሜሪካውን ዓይነት ይመስላል። በአሜሪካ Assemblies of God ከተባሉት የጴንጤቆስጤ እምነት ተከታዮች ተገንጥለው እንደወጡ በአገራችን ያሉትም ከሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን ምእመናን አብረው ሲያመልኩ ቆይተው በኋላ በሥላሴ ክህደታቸው ተገንጥለው የወጡ ናቸው። ለዚህ ክህደትና መገንጠል አስተዋጽኦ ያደረጉት ቀደም ብለው በሥላሴ ክህደታቸው በአሜሪካን አገር የተገነጠሉ ይገኛሉ።

በእነዚህ ሰዎች ትምህርት ከሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያዎቹ ምእመናን ውስጥ ተገንጥለው ከወጡት መካከል አተክለማርያም ገዛኸኝ ይገኛል።

ተክለማርያም ገዛኸኝ የመጀመሪያውን መጽሐፉን «መለኮታዊ ኃይል» በደረሰ ጊዜ ከሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን እንቅስቃሴ ከጀመሩ ሰዎች ጋር እንደነበር ይነገራል። በኋላ ግን «እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል?» በሚል ርእስ በደረሰው መጽሐፍ ከነፎቶግራፉ እንዳስቀመጠው የሥላሴ ክሃዲ በሆነው ዌንደል በሚባል ሰው ከነ ቤተሰቡ ተጠምቆ የዚህ እምነት ተከታይና መሪ ሆነ።

በአሁኑ ጊዜ የዚህ የእምነት ተከታዩች በተለይም የወንጌላዊያን አብያተ ክርስቲያናት በተስፋፋበት አካባቢዎች ማለት በደቡብ ኢትዮጵያ በምዕራብ ኢትዮጵያና በአዲስ አበባ ከተማ /በመጠኑ/ ይገኛሉ።

ዋናው ትምህርታቸው ከላይ እንደገለጽነው በሐዋ. 2፥38 ሐዋርያት በተናገሩት መሠረት ንስሐ ገብቶ «በኢየሱስ ስም» ብቻ በመጠመቅ በመንፈስ ቅዱስ

መምሳት ያድናል እንጂ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ማለት በምሳሌ ስም መጠመቅ አያድንም የሚል ነው። እነዚህ ሰዎች ከላይ እንደገለጽነው የእግዚአብሔርን ቃል ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ሳያመሳክሩ ሉቃስ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ እንደ ጻፈው ሐዋርያው ማቴዎስም ከሞት የተነሣውን ጌታ ትእዛዝ /ማቴ. 28፥20/ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ እንደጻፈው ቢረዱ ሁለቱን ጥቅሶች ወደ ማቃረንና አንደኛው የጥምቀት ፎርሙላ ብቻ የሚያድን ነው ብለው ወደ መመጻደቅ ባልገቡ ነበር። ኧረ ለመሆኑ የኢየሱስ ስም አያድንም ያለ ክርስቲያን ማን ነው? የምንቃመንበት፥ ሕይወቱን ስለኃጢአታችን አሳልፎ የሰጠ ጌታ እርሱ አይደለምን? በትንሣኤውም በሞት ላይ ድልን ያጐናጸፈን እርሱ አይደለምን?

እግዚአብሔር ከሞት አስነሥቶት፥ በአባቱ ቀኝ ከፍ ከፍ ብሎ መንፈስ ቅዱስን ለምእመናን ያፈሰሰ እርሱ አይደለምን? «ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ። እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ» ባለው በጌታ ትእዛዝ መሠረት ስለተጠመቅን ጠፍተናል ማለት ነው? ጌታን የሚያምኑ፥ በቃሉ መሠረት የሚሠሩና የሚኖሩ ካሉ ጠፍታችኋል የሚል ካለ የጌታ ወዳጆች ጠላት መሆኑን አንስተውም።

እንደእነዚህ ሰዎች አባባል ከሆነ በ1914 ዓ.ም የዚህ እምነት ተከታዮች ከተንቀሳቀሱበት ጊዜ በፊት በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም የተጠመቁ ክርስቲያኖች፥ የቤተ ክርስቲያን አበውና ሰማዕታት ሁሉ ጠፍተዋል ማለት ነው። እነዚህ ሰዎች «በኢየሱስ ስም» ብቻ

በመጠመቃቸው በእግዚአብሔር ዘንድ ተወዳጅነትን ለማግኘት የወሰኑ ይመስላሉ። እኛን ግን የወደደን እርሱ እንጂ እኛ አይደለንም። «እግዚአብሔር እርሱ ራሱ እንደ ወደደን ስለኃጢአታችንም ማስተስሪያ ይሆን ዘንድ ልጁን እንደ ላከ እንጂ እኛ እግዚአብሔርን እንደ ወደድነው አይደለም።» 1ዮሐ. 4፥10። እግዚአብሔር እኛን የወደደን ስለመልካም ሥራችን፥ ስለፎርሙላችን ጥራትም አይደለም። ሮሜ 3፥24።

የዚህ እምነት ተከታዮች የቤተ ክርስቲያናችን አሠራር በሐዋርያት ሥራ በተገለጸው ፎርሙላ መሠረት ማጥመቅ ነው ብለው ወንጌል ወዳልደረሰባቸው ቦታዎች የክርስቶስን የጸጋ ወንጌል ቢያደርሱና ቢሸከሙ መልካም ነበር። ነገር ግን ከላይ በተጠቀሰው ሥውር የመመጻደቅና የትዕቢት ትምህርታቸው ምክንያት «የኢየሱስ ስም» እንደ ምትሐትና ድግምት ተጠርቶ ሰው ካልተጠመቀ በቀር ሊድን አይችልም ስለሚሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ተጠምቆ በጌታ ያመነ ክርስቲያን ዳግም መጠመቅ አለበት ይላሉ።

ከዚህ የተነሣ /የደኅንነት/ የወንጌል ሰባኪዎች ሳይሆኑ የፎርሙላ ወይም የሕግ ሰባኪዎች ሆነዋል። በሕግ ስብከታቸውም ያልጸኑትን ነፍሳት በማስፈራራትና በማናወጥ በክርስቶስ ያገኙትን ነፃነት ተጠቃሚዎች እንዳይሆኑ ባሪያዎች ሊያደርጓቸው ሞክረዋል። «የጸጋም ስጦታ ልዩ ልዩ ነው ጌታም አንድ ነው፤ አገልግሎትም ልዩ ልዩ ነው ጌታም አንድ ነው፤ አሠራርም ልዩ ልዩ ነው፥ ሁሉን በሁሉ የሚያደርግ እግዚአብሔር ግን አንድ ነው» 1ኛ ቆሮ. 12፥4-6 በሚለው ቃል መንፈስ ቢመሩ ኖሮ አሁን ወዳሉበት መመጻደቅ ሳይደርሱ ሁሉንም በክርስቶስ ፍቅር ለመቀበል በቻሉ ነበር።

## ምዕራፍ ስድስት።

# በሥላሴ ስም መጠመቅ በጥንት ቤተ ክርስቲያን።

ያአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ተሰባስበው አንድ መልክ እስኪይዙ ድረስ የነበሩ የሐዋርያት ደቀመዛሙርትና አበው፥ በዚያን ጊዜ ስለነበረው የቤተ ክርስቲያን ሥነ ሥርዓትና አምልኮ የጻፏቸው ጽሑፎች አሉ። እነዚህ ጽሑፎች በጊዜው ስለነበር የቤተክርስቲያን የጥምቀት አፈጻጸም ምን እንደሚሉ ከዚህ ቀጥሎ እንመለከታለን፦

አንዳንዶች በስሕተት በሥላሴ ማመንና በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ማጥመቅ ከኒቂያ ጉባኤ /325 ዓ.ም/ በኋላ የመጣ ነገር ነው ብለው ያስተምራሉ። ከዚህም ሌላ ይህ ጉባኤ ብቻውን የሆነውን የኢየሱስን አምላክነት በማጉደፍ በድምፅ ብልጫ ሦስት እግዚአብሔሮች አሉ ብሎ ወሰነ ይላሉ። ይህ ግን ታሪክን ማዛባትና በትክክል አለመረዳት ነው። ለራስ ሐሰትን በመቀበል ተሳስቶ ሌሎችን ማሳሳት ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ የኒቂያ ጉባኤ የእምነት መግለጫ በተቃራኒው፥ ክርስቶስን ፍጡር ነው ብሎ አምላክነቱን የካደውን የአርዮስን ትምህርት የሚቃወምና ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አንድ መለኮት የሆነውን አምላክነቱን የሚያረጋግጥ ነው።

## ዲዳኬ።

በጥንት ቤተ ክርስቲያን ሥነ-ሥርዓት በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ማጥመቅ በማቴ. 28፥20 ከተገለጸው ሌላ ዲዳኬ በሚባል ጽሑፍ ላይ ተጽፎ

ይገኛል። ይህ ጽሑፍ ከአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን አካባቢ የተገኘ ሲሆን ከ100 ዓ.ም ቀደም ብሎ እንደተደረሰ ይታመናል። ዲዳኬ ስለጥምቀት የያዘው ሙሉ ቃል እንደሚከተለው ነው:-

«ጥምቀትን በሚመለከት እንደሚከተለው አጥምቁ:- መባል ያለበትን ካላችሁ በኋላ በወራጅ ውኃ /ወንዝ/ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቁ። ተንቀሳቃሽ /ወራጅ/ ውኃ ከሌላችሁ በሌላ ውኃ አጥምቁ፤ በቀዝቃዛ ውኃ ካልቻላችሁ ለብ ባለ ውኃ አጥምቁ። ሁለቱም ከሌላችሁ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም በራስ /ጭንቅላት/ ላይ ሦስት ጊዜ አፍስሱ። ከጥምቀት በፊት አጥማቂው ተጠማቂውና ሌሎች የሚችሉ ሰዎች ይጹሙ። ተጠማቂው ግን በምንም ዓይነት መንገድ መጾም አለበት። በጌታ ስም ከተጠመቀ በስተቀር ማንም ከቅዱስ ቁርባን አይብላ፥ አይጠጣ።»

እነሆ ዲዳኬ ስለጥምቀት አንድ ዓይነት የአሠራር መንገድ ሳይሆን እንደሁኔታውና አመቺነቱ የአሠራር ነፃነት ይሰጣል። ይኸኛው ዓይነት የጥምቀት አፈጻጸም ትክክል ነው ያኛው ዓይነት ስሕተት ነው ሳይል ምእመናን ለእነርሱ አመቺ በሆንና በመረጡት መንገድ እንዲያጠምቁ የአፈጻጸም ምርጫ ሰጥቷል። በዲዳኬ የተገለጸውን ልምምድ በአሁኑም ዘመን መመልከቱ ለአብያተ ክርስቲያናት ኅብረት ጠቃሚ ሊሆን ይችላል።

ነገር ግን /ከሁሉም በላይ/ ጥምቀቱ «በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም» እንደሚደረግ ሁለት ጊዜ ይጠቅሳል። በመጨረሻም በጌታ ስም ከተጠመቀ በስተቀር ከቅዱስ ቁርባን ማንም መብላት እንደሌለበትም ይናገራል። እነሆ ዲዳኬ «በጌታ ስምና» በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ተቃራኒነት ወይም ግጭት አልፈጠረም። ምእመናን በመጀመሪያው መቶ ዓመት «በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም» ይጠመቁ ነበር።

ዮስቲንዮስ ሰማዕት።

በማያወላውል ምስክርነቱ ምክንያት ሰማዕት ሆኖ በ165 ዓ.ም በሮም የሞተው ዮስቲንዮስ በክርስቲያኖች ላይ የሚፈጸመው ስደት ትክክል አለመሆኑን በማስረዳት በ155 ዓ.ም አካባቢ አንቶኒዮስ ለተባለው ሮማዊ ንጉሠ ነገሥት የመጀመሪያውን የመልስ የመከላከያ ደብዳቤ ጽፎአል። በዚህ የመከላከያ ደብዳቤው ውስጥ ክርስቲያኖች እንዴት አዲስ ሰዎች እንደሆኑ ሲገልጽ የሚከተለውን ይጽፋል።

«ከዚህ ቀጥሎ ራሳችንን እንዴት ለእግዚአብሔር አሳልፈን እንደሰጠንና በክርስቶስም አዲስ ሰዎች እንደተደረግን ልገልጽልህ እፈልጋለሁ። የምናስተምራቸው ነገሮች እውነት እንደሆኑ ተረድተውና አምነው፥ በተማሩት መሠረት ኑሮአቸውን ያስተካክሉ ሰዎች ካሉ በጾምና በጸሎት እግዚአብሔርን የኃጢአታቸውን ይቅርታ እንዲጠይቁ ትምህርት ይሰጣቸዋል። ከዚያ በኋላ ውኃ ወዳለበት እንወስዳቸውና ቀደም ብለን እኛው ራሳችን አዲስ በተወለድንበት መንገድ እነርሱም አዲስ ይወለዳሉ። ይኸውም የሚሆነው በውኃ ውስጥ የሁሉ ጌታና አምላክ በሆነው በአብ፥ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስና በመንፈስ ቅዱስ ስም ሲታጠቡ ነው።

አዲስ ለመወለድ ፈልጎ ኃጢአቱን የሚናዘዘው ሰው ላይ የሁሉ አባትና ጌታ የሆነው ስም ይጠራለታል። ይህ ስም የሚጠራው በአጥማቂው ብቻ ነው። ድንቅ የሆነውን የአምላክን ስም ማንም ሊጠራው አይችልም። ማንም በድፍረት አደርጋለሁ የሚል ካለም አእምሮውን የሳተ መሆን አለበት። ይህ ጥምቀት ብርሃን ሕይወት ወይም የሕይወት መታደስ ይባላል። ምክንያቱም እነዚህን ነገሮች የሚለማመዱ አእምሮአቸው ስለሚታደስ ነው። የሚታደሰው ሰው በጴንጤናዊ ጲላጦስ ዘመን በተሰቀለው

በኢየሱስ ክርስቶስ ስምና በነቢያት አማካይነት ስለኢየሱስ ሁሉን አስቀድሞ በተናገረ በመንፈስ ቅዱስ ስም ይጠመቃል።

አምና፥ ፈቃደኛ የሆነውን ሰው በዚህ መልክ ካጠመቅነው በኋላ «ወንድሞች» የተባሉት ተሰብስበው ወዳሉበት እንወስደውና ከልብ የሆነ የጋራ ጸሎት ስለራሳችን፥ አዲስ ስለተጠመቀውና /በየሥፍራው ላሉ/ ሰዎች ሁሉ እናደርጋለን። ጸሎቱ እውነትን በመያዝ በኑሮአችን ጥሩና ታዛዥ ዜጎች እንድንሆንና የዘላለምን ሕይወት የምናገኝ እንድንሆን ነው።»

እነሆ ሰማዕቱ ዩስቲኖስ በሁለተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ማለት 150 ዓ.ም አካባቢ የነበሩ አብያተ ክርስቲያናት ጥምቀታቸውን እንዴትና በማን ስም እንደሚያደርጉ በግልጽ አስቀምጦአል። አዲስ ልደት የሚሆነው «የሁሉ ጌታና አምላክ በሆነው በአብ፤ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስና በመንፈስ ቅዱስ ስም ሲታጠቡ ነው»። ከዚያም ቀጥሎ ባለው ክፍል፤ የሁሉ አባት የሆነውን አብን፥ መድኃኒታችንን ኢየሱስ ክርስቶስንና መንፈስ ቅዱስን አንድ በአንድ በመግለጽ በዘመኑ ምእመናን ዘንድ ጥምቀት በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እንደተደረገ ያረጋግጥልናል። እነዚህ ጌታ ባዘዘው መሠረት በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ተጠምቀው በከፍተኛው ስደት ዘመን በካታካምቡና በየጥሻው እየኖሩ ሕይወታቸውን መሥዋዕት አድርገው ስለክርስቶስ ምስክርነት ሰጥተዋል። እኛም በአብ በወልድና በመንፈቅ ቅዱስ ስም የተጠመቅን ፈለጋቸውን የተከተልን ነን።

አቡሊደስ።

አቡሊደስ በ215 ዓ.ም በሮም ከተማ የነበረ ጳጳስ ነው። ይህ ጳጳስ ቤተ ክርስቲያን ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ የምትከተላቸውንና የምትጠቀምባቸውን ሥነ-ሥርዓቶች

«የሐዋርያት ሥነ-ሥርዓት/ልምድ/» በተባለው መጽሐፉ በሰፋት ዘርዝርአል። በዚህ መጽሐፍ ስለጥምቀት አፈጻጸም ከጻፈው የሚከተለውን ክፍል ብቻ እንጠቅሳለን።

«....ከዚህ በኋላ በውኃ ውስጥ ወደ ቆመው የቤተ ክርስቲያን ካህን ተጠማቂው ይሰጥ። ሁላቸውም በውኃው ውስጥ ልብስ ሳይለብሱ ራቁታቸውን ይቆሙ። እንዲሁም አንድ ዲያቆን ከካህኑ ጋር ወደ ውኃው ውስጥ ይገባ።

ወደ ውኃው ውስጥ ሲገባ አጥማቂው፡- በተጠማቂው ላይ እጁን በመጫን፤ ሁሉን በሚችል በእግዚአብሔር አብ ታምናለህን? ብሎ ይጠይቀዋል። ተጠማቂው፡- አዎን፥ አምናለሁ ብሎ ይመልሳል። እጁን በራሱ ላይ እንደጫነ አንድ ጊዜ ያጠምቀዋል። ከዚያ በኋላ አጥማቂው፤በእግዚአብሔር ልጅ በክርስቶስ ኢየሱስ ከመንፈስ ቅዱስ በተፀነሰ ከድንግል ማርያም በተወለደ በጴንጤናዊው ጲላጦስ ዘመን በተሰቀለ፤ በሞተ በሦስተኛው ቀን ከሙታን መካከል በተነሣና ወደሰማይ ባረገ በእግዚአብሔር አብ ቀኝ በተቀመጠ በሕያዋንና በሙታን ሊፈርድ በሚመለስ ታምናለህን? ብሎ ይጠይቀዋል። ተጠማቂው፡- አዎን፥ አምናለሁ፡- ይላል። አምናለሁ ብሎ ሲመልስ ለሁለተኛ ጊዜ ይጠመቅ፡- እንደገና አጥማቂው፡- በመንፈስ ቅዱስ በቅድስት ቤተ ክርስቲያን በሥጋ ትንሣኤ ታምናለህን? ብሎ ይጠይቀው፡-

ተጠማቂው፡- አዎን፥ አምናለሁ ይበል። ከዚያ በኋላ ሦስተኛ ጊዜ ያጥምቀው፡-

ተጠማቂው ከውኃው ውስጥ በሚወጣበት ጊዜ በምስጋና ዘይት ይቀባል። ከዚያ በኋላ እያንዳንዱ ተጠማቂ ሰውነቱን አድርቆ ልብሱን በመልበስ አዲስ ከተጠመቁ ጋር በአንድነት ይሰበሰባል።»

የአቡሊደስ የጥምቀት ሥነ ሥርዓት ስፋ ያለና ዝርዝር ሁኔታዎችን የሚገልጽ ነው። ለኛ ግን እያንዳንዱ ተጠማቂ መጀመሪያ በአብ፥ ቀጥሎ በልጁ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በመጨረሻም በመንፈስ ቅዱስ ማመኑን መጠየቁ እጅግ የሚያስገርመን ነው። ተጠማቂው በአብ፥ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ማመኑን ተራ በተራ እየመሰከረ ሦስት ጊዜ /በውኃ ውስጥ/ ይጠመቅ ነበር ማለት ነው። ጥምቀቱ የሚያልቀው በአብ ብቻ አምኖ በመጠመቁ ብቻ ሳይሆን፥ ወይም በእግዚአብሔር ልጅ በክርስቶስ ኢየሱስ ብቻ አምኖ በመጠመቁ ሳይሆን እንዲሁም በመንፈስ ቅዱስ ብቻ አምኖ ሲጠመቅ ሳይሆን፡- በሦስቱም ማለት በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ማመኑን ገልጾ በሦስቱም ስም ሲጠመቅ ነው። የጥንት ክርስቲያኖች በዚህ መልክ ይጠመቁ ነበር።

## ጠርጡሊያኖስ /160-215 ዓ.ም/።

ጠርጡሊያኖስ በጣም ከታወቁ የጥንት ቤተ ክርስቲያን አበው አንዱ ነው። በሕይወቱ ዘመን ስለሥላሴ፥ ንስሐና ጥምቀት ስለሌሎችም ብዙ ጉዳዮች ጽፎአል። ስለጥምቀት ሰፋ አድርጎ ከጻፈው የሚከተሉትን ብቻ እንመለከታለን፡-

«ወደ ውኃው ውስጥ በደረስን ጊዜ፥ ቀደም ብሎ በጳጳሳት ዘመን ሥልጣን እንደነበረው፥ ሰይጣንን፥ ከፉ ሥራውንና መላእክቱን መካዳችንን እናረጋግጣለን። ከዚያ በኋላ፥ ጌታችን በወንጌሉ ካዘዘው ሰፋ በሚል ቃል፥ ለምንጠየቀው መልስ እየሰጠን ሦስት ጊዜ በውኃው ውስጥ እንጠመቃለን፡- ከዚያ በኋላ ወደ ጉባኤው ተቀብለውን የወተትና የማር ቅልቅል ይሰጡናል። ከዚያ ዕለት ጀምሮ ለአንድ ሳምንት ከዕለታዊ እጥበት እንቆጠባለን።» ካለ በኋላ፡-

«የጥምቀት ሕግ ወይም ደንብ ተደንግጎአል። የታዘዘውም ደንብ፦ ሂዱ ካለ በኋላ፥ አሕዛብን በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው አስተምሯቸው» ማቴ. 28፥19 የሚል ነው ብሎ ይጽፋል።

እነሆ ጠርጡሊያኖስ ቀደም ብሎ «ለምንጠየቀው ጥያቄ መልስ እየሰጠን ሦስት ጊዜ በውኃው ውስጥ እንጠመቃለን» ማለቱ በአቡሊዲስ ሥርዓት እንደተገለጸው በአብ፥ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ማመናቸውን እየመሰከሩ አንድ በአንድ መጠመቃቸውን በማመልከት ነው። ቀጥሎም ጥምቀትን ለመፈጸም የታዘዘው ፎርምና ሕግ ጌታ በማቴዎስ ወንጌል 28፥19 እንዳዘዘው «በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም» ማጥመቅ ነው ብሎ በማያሻማ ቋንቋ ይገልጻል።

እስካሁን የጠቀስናቸው የጥንት ቤተ ክርስቲያን ምስክሮች በምን ዓይነት መንገድና ስም በዘመኑ የነበሩ ምእመናን ይጠመቁ እንደነበር ለማሳየት ለአብነት ያክል ነው እንጂ ምስክሮችን አንድ በአንድ በመጥቀስ እስከዘመናችን ለመድረስ ይቻላል። የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን በዘመናት ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ተከልላና ተጠምቃ ኖራለች።

## የቤተ ክርስቲያን የእምነት መግለጫዎች።

በየጊዜው የሚነሡ የሐሰት መምህራን የእግዚአብሔርን ቃል በስሕተት እየተረጐሙ ምእመናንን ስለሚያሳስቱ ቤተ ክርስቲያን የእምነት መግለጫዎች አውጥታለች። በእነዚህ የእምነት መግለጫዎች በሥላሴ ማመንን መግለጽ መሠረታዊ የእምነት መግለጫ ሆኖ ይገኛል። በመግለጫዎቹ መሠረት በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ማመኑን የማይመሰክር ሊጠመቅና የቤተ ክርስቲያን አባል ሊሆን አይችልም። ከእነዚህም

የእምነት መግለጫዎች ቀደምትነት ያላቸውና የዓለም አቀፍ ቤተ ክርስቲያን እንደሆኑ የሚታወቁ፣ የሐዋርያት፣ የኒቂያና የአትናቴዎስ የእምነት መግለጫዎች ናቸው። የዓለም አቀፍ ቤተ ክርስቲያን ተብለው የሚታወቁበትም ምክንያት «ከመናፍቃን በስተቀር» አብዛኛዎቹ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት /የእግዚአብሔርን ቃል /ትምህርት በትክክል እንደሚያብራሩ በመቀበል የእምነታቸው መግለጫ ስላደረጉ ነው።

## የሐዋርያት የእምነት መግለጫ።

የሐዋርያት የእምነት መግለጫ፣ መልኩ ሐተታ ከመሆን በስተቀር በጥያቄ መልክ ከላይ ከቀረበው ከአቡሊደስ የጥምቀት ሥነ ሥርዓት ጋር አንድ ነው። መናገር የማይችሉ የምእመናን ልጆች ካልሆኑ በስተቀር መናገር የሚችሉ ሁሉ በሐዋርያት የእምነት መግለጫ መሠረት በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ማመናቸውን ከመሰከሩ በኋላ ይጠመቁ ነበር። የቤተ ክርስቲያን አባቶች ቅዱስ አይሬኒዎስና /190/ ጠርጡሊያኖስ እንደመሰከሩ ይህ እምነት ቤተ ክርስቲያን ከሐዋርያት የተቀበለችውና ከመጀመሪያው ጀምሮ የነበረ ነው።

## የኒቅያ የሃይማኖት መግለጫ።

የኒቅያ የሃይማኖት መግለጫ በ325 ዓ.ም በኒቅያ ላይ በዋለው ጉባኤ ተነድፎ በ381 ዓ.ም ከብዙ ጥናት በኋላ ወደ ፍጻሜ የደረሰ የእምነት መግለጫ ነው። የኒቂያ የሃይማኖት መግለጫ የወጣው ክርስቶስ ፍጡር ነው ብሎ የጌታችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት የካደውን የአርዮስን ትምህርት ለመቃወም ነው። በመግለጫው ውስጥ ክርስቶስ ኢየሱስ ፍጹም አምላክ መሆኑንና ፍጡር አለመሆኑን የሚገልጹ ኃይለ ቃላት በተለይም በሁለተኛው አንቀጽ ሠፍረው ይገኛሉ።

እነዚህም «ዓለም ሳይፈጠር ከአብ በተወለደ፥ ከአምላክ በተገኘ አምላክ፥ ከብርሃን በተገኘ ብርሃን፥ ከእውነተኛ አምላክ በተገኘ እውነተኛ አምላክ፥ በህልውናው ከአብ ጋር አንድ የሆነ፥ በተፈጠረ ሳይሆን በተወለደ...» የሚሉ ናቸው።

በሦስቱ አካላት ማለት በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ መካከል ፍጹም እኩልነት እንዳለም መግለጫው ይገልጻል።

የሥላሴ ተቃዋሚዎች ታሪክን በማዛባት ተሳስተው እንደሚያሳስቱት ሳይሆን በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም መጠመቅ ከኒቂያ ጉባኤ /325 ዓ.ም/ በኋላ የተጀመረ ነገር ሳይሆን ቀደም ብሎ እንዳየነው በሁለተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በነአቡሊደስና በነሰማዕቱ ዮስቲንዮስ ዘመን የነበረ ነው። ከዲዳኬና ከነአይሬነዎስ እንደምንረዳው ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ እንደነበርም እንረዳለን። እነዚህ መምህራን ይህ ስሕተታቸውና ውሸታቸው ሳይበቃቸው የኒቂያ ጉባኤ በድምፅ ብልጫ «ሦስት እግዚአብሔሮች አሉ ብሎ ወሰነ» በማለት የመግለጫውን አመጣጥ ከመሠረቱ ያልመረመሩትን ምዕመናን ያሳስታሉ። በውኑ የኒቂያን የእምነት መግለጫ የሚቃወም፥ ያው የአርዮስ ወንድምና ተመሳሳይ መንፈስ ያለው ካልሆነ በስተቀር ሌላ ማን ይሆናል?

እነሆ የኒቂያ የሃይማኖት መግለጫ ወልድ የአብ ልጅ መሆኑንና «በህልውናው ከአብ ጋር አንድ» መሆኑን ይመሰክራል እንጂ ሁለት ህልውና እንዳላቸው አይመሰክርም። መንፈስ ቅዱስም ከአብና ከወልድ ጋር የሚሰገድለት መሆኑን ይመሰክራል እንጂ ለብቻው የራሱ ህልውና እንዳለው አይመሰክርም። ስለዚህ ዲያብሎስ የሐሰት አባት ሐሰትን ሲናገር ከራሱ ይናገራል እንደተባለው የሥላሴ ተቃዋሚዎች ከራሳቸው ፈጥረው

ሐሰትን ካልተናገሩ በስተቀር የኒቂያ የሃይማኖት መግለጫ «ሦስት እግዚአብሔሮች» ብሎ አያስተምርም።

## የአትናቴዎስ የእምነት መግለጫ።

አንዳንዴ «የአጠቃላይ ቤተ ክርስቲያን የእምነት መግለጫ» ተብሎ የሚጠራው የአትናቴዎስ የእምነት መግለጫ ከ381 እስከ 428 ዓ.ም ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ እንደተጻፈ ይታመናል። ቅዱስ አትናቴዎስ እንደጻፈው እስካሁን ማረጋገጫ ባይገኝለትም በይዘቱ የአትናቴዎስንና የኒቂያን እምነት ስለሚያንፀባርቅ «የአትናቴዎስ» ተብሎአል። መግለጫው አርባ ተመጣጣኝ የሆኑ አረፍተ ነገሮችን የያዘ ሲሆን የመጀመሪያዎቹ ሃያ ስድስት /26/ አረፍተ ነገሮች ቤተ ክርስቲያን ስለሥላሴ አንድነትና ሦስትነት የምታምነውን የሚናገሩ ናቸው። ከሃያ ሰባት እስከ አርባ ያሉት አረፍተ ነገሮች ደግሞ ስለክርስቶስ ባሕርይ የሚናገሩ ናቸው።

መግለጫው ደኅንነት ከትክክለኛ እምነት ጋር የተያያዘ መሆኑንና፣ በትክክል አለማመን ደግሞ ወደ ጥፋት እንደሚመራ በመግለጽ እግዚአብሔር አንድ መለኮት ሦስት አካላት እንዳለው ያሳያል። በመግለጫው መሠረት እግዚአብሔር በህልውናው አይከፋፈልም። እግዚአብሔር አንድ ነው። ሦስቱ «አካላት» አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ግን አይደበላለቁም። መግለጫው ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ፣ በተለይ ስለሥላሴና ትስብእት በደንብ ስለሚያብራራ ሙሉ ቃሉን እንደሚከተለው አስፍረናል።

የአትናቴዎስ መግለጫ ሙሉ ቃል፡-

1. ለመዳን የሚፈልግ ሁሉ ከሁሉም ነገር አስቀድሞ የሁሉ የሆነች የቤተ ክርስቲያንን ሃይማኖት እውነተኛ አድርጎ ሊቀበል ያስፈልገዋል።

2. ንጹሕና ሙሉ አድርጎ ያልጠበቀው ሁሉ ያለ ጥርጥር የዘላለም ጥፋት ይደርስበታል።

3. በሦስትነቱ አንድነቱን በአንድነቱም ሦስትነቱን አምነን አንድ አምላክን እናመልካለን። ይህም እውነተኛ የክርስትና ሃይማኖት ነው።

4. ይህንንም የምናደርገው አካላቱን ሳንደባልቅ መለኮታዊ ህልውናውንም ሳንከፍል ነው።

5. ምክንያቱም የአብ አካል ለብቻው የወልድ ለብቻው የመንፈስ ቅዱስም ለብቻው ስለሆነ ነው።

6. ሆኖም የአብ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ መለኮት አንድ ነው ክብሩ ሥልጣኑም እኩል ሆኖ ይኖራል።

7. ወልድ በህልውናው እንደ አብ ነው መንፈስ ቅዱስም እንደዚሁ ነው።

8. አብ አልተፈጠረም ወልድ አልተፈጠረም መንፈስ ቅዱስም አልተፈጠረም።

9. አብ ወሰን የለውም ወልድ ወሰን የለውም መንፈስ ቅዱስም ወሰን የለውም።

10. አብ ዘላለማዊ ነው ወልድ ዘላለማዊ ነው መንፈስ ቅዱስም ዘላለማዊ ነው።

11. ቢሆንም ዘላለማዊ የሚሆን አንድ እንጂ ሦስት አይደሉም።

12. ያልተፈጠረና ወሰን የሌለው ሦስት እንደሆን እንደዚሁም ያልተፈጠረና ወሰን የሌለው አንድ ነው።

13. እንዲሁም አብ ሁሉን የሚችል ነው ወልድ ሁሉን የሚችል ነው መንፈስ ቅዱስም ሁሉን የሚችል ነው።

14. ቢሆንም ሁሉን የሚችል አንድ እንጂ ሦስት አይደለም።

15. ስለዚህ አብ አምላክ ነው ወልድ አምላክ ነው መንፈስ ቅዱስም አምላክ ነው።

16. ሆኖም አንድ አምላክ እንጂ ሦስት አማልክት አይደሉም።

17. ስለዚህ አብ ጌታ ነው፥ ወልድ ጌታ ነው፥ መንፈስ ቅዱስም ጌታ ነው።

18. ሆኖም፥ አንድ ጌታ እንጂ ሦስት ጌቶች አይደሉም።

19. ምክንያቱም የክርስትና እምነት እውነተኛነት እያንዳንዱ አካል አምላክና ጌታ መሆኑን እንድናምን እንደሚያስገድደን ሁሉ፥ የክርስትና ሃይማኖት ሦስት አማልክት ወይም ሦስት ጌቶች እንዳንል ይከለክለናል።

20. አብ በማንም አልተሠራም፥ አልተፈጠረም፥ አልተወለደምም።

21. ወልድ ከአብ ተወለደ እንጂ አልተሠራም፥ አልተፈጠረምም።

22. መንፈስ ቅዱስ አልተሠራም አልተፈጠረም አልተወለደምም፥ ነገር ግን ከአብና ከወልድ የሚሠርጽ ነው።

23. ስለዚህ አብ አንድ ስለሆነ ሦስት አብ አይደለም፥ ወልድም አንድ እንጂ ሦስት ወልድ አይደለም፥ መንፈስ ቅዱስም አንድ እንጂ ሦስት አይደለም።

24. ከሦስቱ አካላት አንዱ ከሌላው ቀዳሚነት ወይም ደኅረኔት የለውም፤ አንዱም ከሌላው የሚበልጥ ወይም የሚያንስ አይደለም።

25. ስለ ሆነም፥ ሦስቱ አካላት በእኩልነትና በዘላለማዊነት አንድ ናቸው። ከዚህ የተነሣም ከፍ ብሎ እንደ ተጠቀሰው ሦስቱ አካላት በአንድ መለኮት አንድ አምላክም በሦስት አካላት ይመለካል።

26. ለመዳን የሚፈልግ ሁሉ ስለ ሥላሴ እንደዚህ ማሰብ ይገባዋል።

27. ከዚህም ሌላ የዘላለምን ደኅንነት ለማግኘት የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን በሥጋ መገለጽ በእውነት ማመን አስፈላጊ ነው።

28. ምክንያቱም ትክክለኛው እምነት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ አምላክም ሰውም መሆኑን አምነን ማስታወቅ ነው።

29. እርሱም ከዘመናት አስቀድሞ ከአብ የተወለደ አምላክ፥ ከእናቱም በሥጋ በዓለም የተወለደ ሰው ነው።

30. የሚያስብ ነፍስ ያለችውና የሰውን ሥጋ የለበሰ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው ነው።

31. በአምላክነቱ ከአብ ጋር የተካከለ፥ በሰውነቱም ከአብ ያነሰ ነው።

32. አምላክም ሰውም ቢሆንም አንድ ክርስቶስ እንጂ ሁለት ክርስቶስ አይደለም።

33. አንድ ነው ስንል ግን የሰውን ሥጋ ለበሰ እንጂ መለኮትን ወደ ሥጋ አልለወጠም።

34. በእርግጥ አንድ የሆነውም በባሕርያት መደባለቅ ሳይሆን፥ በአካል አንድ በመሆኑ ነው።

35. ምክንያቱም የሚያስብ ነፍስና ሥጋ አንድ ሰው እንደሆነ ሁሉ አምላክና ሰው በክርስቶስ አንድ ናቸው።

36. እርሱም ለደኅንነታችን ሲል መከራ የተቀበለ፥ ወደ ሲኦል የወረደ፥ ከሙታን የተነሣ፤

37. ወደ ሰማይ የወጣ፥ በአብ ቀኝ የተቀመጠ፥ በሕያዋንና በሙታንም ሊፈርድ ከዚያ የሚመለስ፥

38. በመምጣቱ ጊዜም ሰዎች ሁሉ በሥጋ ተነሥተው ስለ ሥራቸው መልስ ይሰጣሉ።

39. መልካም የሠሩ ወደ ዘላለም ሕይወት፥ ክፉ የሠሩም ወደ ዘላለም እሳት ይገባሉ።

40. ይህ እውነተኛው የክርስትና እምነት ነው። ይህን የማያምንና አጥብቆ የማይዝ ሊድን አይችልም።

ምዕራፍ ሰባት።

# የሐሰት ትምህርቶች /እምነቶች/ ባሕርያት።

በሥላሴ ብቻ ሳይሆን በተለያዩ የእምነት አንቀጾች የሐሰት ትምህርት የሚያስተምሩ አሉ። እነዚህ ሁሉ የሐሰት ትምህርቶች ተመሳሳይ ባሕርያት አሉአቸው። እነዚህን ጠባያት አውቆ ማንነታቸውን መለየትና ለራስና ለሌሎች መጠንቀቅ በጣም አስፈላጊ ነው።

## 1. አዲስና ልዩ እውነት ተገለጠልኝ፥

የሐሰት ትምህርት መምህራን አብዛኛውን ጊዜ እግዚአብሔር ለእነርሱ የተለየ ነገር እንደገለጠ ይናገራሉ። አብዛኛውን ጊዜ ይህ ተገለጠልኝ የሚሉት እውነት፥ ከዚህ ቀደም ተገልጦ የማያውቅና ቀደም ብለው ከተሰጡት መገለጦች ሁሉ የሚበልጥ ወይም እነርሱን የሚቃረን ነው። በተጨማሪም ከእግዚአብሔር ቃል /ከመጽሐፍ ቅዱስ/ ሌላ እምነታቸውን የሚመሠርቱበት ሌላ መመሪያ አለን ይላሉ። እኛ ግን እንደ ቤተ ክርስቲያን፥ ትምህርቶቻችንንና አሠራራችንን በማይሳሳተው በእግዚአብሔር ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ መመዘን አለብን፥

## 2. አዲስና ልዩ አተረጓጎም፥

አንዳንድ የሐሰት መምህራን አዲስና ልዩ እውነት ተገለጠልን ባይሉም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውን ምሥጢር የሚፈታ የአተረጓጎም ቁልፍ ይዘናል ይላሉ። ትርጓሜአቸው በቤተ ክርስቲያን ሲወርድ ሲዋረድ

ከቆየውና ከኖረው ትርጓሜ /መረዳት/ የሚለይ ነው። መጽሐፍ ቅዱስን አብዛኛውን ጊዜ የራሳቸውን ትምህርት ለመደገፍ አገባቡንና ቅደም ተከተሉን ሳይከተሉ ይተረጉሙታል። በተለይም በሐሰት ትምህርቱ መሪ አተረጓጎምና አመለካከት ተከታዮቹ ይመራሉ።

## 3. ከመጽሐፍ ቅዱስ የሚለይ /ሌላ/ መመሪያ አላቸው፥

አንዳንድ የሐሰት ትምህርቶች ከመጽሐፍ ቅዱስ ይበልጣሉ ብለው የሚገምቱአቸው መጻሕፍት አሏቸው። መጽሐፍ ቅዱስ ከጊዜ በኋላ የተለወጠና ስሕተት የተጨመረበት መጽሐፍ ነው ይላሉ። ሌሎቹ ደግሞ ግልጽ የሆነውን የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት ሳይሆን የመሪያቸውን ትርጓሜ አልቀው ያያሉ።

## 4. ሌላ ኢየሱስ፥

በሁሉም የሐሰት ትምህርቶች የሚገኝ አንድ ጠባይ፤ ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት ቤተ ክርስቲያን ስታስተምር ከቆየችው የተለየ፤ የተሳሳተ ትምህርት ማስተማር ነው። የሐሰት ትምህርቶች ኢየሱስ መጽሐፍ ቅዱስ ከሚያስተምረው፥ ሥጋ ለብሶ በምድር ከኖረና ስለኃጢአታችን ከሞተ ከዘላለማዊው አምላክ ያነሰ ነው ይላሉ። የእምነታቸው ይዘት ምንም ዓይነት ይሁን የሐሰት ትምህርቶች በአጠቃላይ የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት ይክዳሉ።

## 5. ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ ያላቸው ትምህርት፥

ሥላሴን ሙሉ በሙሉ ይክዳሉ ወይም ያልተሟላ ትምህርት ያስተምራሉ። አንድ አምላክ ሦስት አካላት

የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት የአረመኔ ወይም የሰይጣን ትምህርት ነው በማለት ይቃወማሉ።

## 6. ተለዋዋጭ ትምህርተ መለኮት አላቸው፤

ተስፋቸውን የሚጥሉበት እውነተኛ ቋሚ መሠረት ስለሌላቸው ትምህርታቸውን በየጊዜው ይለዋውጣሉ። ተከታዮቻቸውም የተማሩት ትምህርት ተለውጦ ወይም በሚበልጥ መገለጥ ተሸር ያገኙታል። ለምሳሌ ቀደም ብሉ የያህዌ ምስክሮች ክትባት ኃጢአት ነው ብለው ያምኑ ነበር። አሁን ግን ይህ ትምህርት ቀርቶአል።

## 7. ጠንካራ መሪ አላቸው፤

አብዛኛውን ጊዜ የሐሰት ትምህርቶች ራሳቸው የእግዚአብሔር መልእክተኞችና ከእርሱ ጋር ልዩ ግንኙነት አለን በሚሉ ማዕከላዊ መሪዎች ይመራሉ። መሪው ከእግዚአብሔር ጋር ልዩ ግንኙነት አለኝ ስለሚል የሐሰት ትምህርቱን ይዘትና ጠባይ የመወሰን ኃይል አለው። ከዚህም የተነሣ በተከታዮቹ ላይ ከፍተኛ ሥልጣንና ተጽእኖ አለው።

ይህ ጠንካራ መሪነት ተከታዮቹ ሙሉ በሙሉ በእምነት በጠባይና፣ በኑሮ ዘይቤ በሐሰት ትምህርቱ እንዲደገፉ ያደርጋቸዋል። በተለይም መሪነቱ መጥፎና ብልሹ በሆነ ሰው እጅ ከሆነ በዘመናችን በአሜሪካን አገር በተደጋጋሚ እንደታየው ወደ አደገኛ /አሳዛኝ/ ፍጻሜ ሊደርስ ይችላል።

## 8. በሥራ መዳን፤

በሐሰት ትምህርቶች ሁሉ የማይገኝ አንዱ ትምህርት የእግዚአብሔር የጸጋ ወንጌል ነው። ማናቸውም ቢሆኑ ሰው ከዘላለም ፍርድ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ብቻ እንደሚድን አያስተምሩም። በክርስቶስ ማመንን

የሚያስተምሩ ከሆኑም ለመዳን በተጨማሪ «ይህን አድርግ»፥ «ያንን ተከተል» ይላሉ። ሁሉም የሐሰት ትምህርቶች በጸጋ የመዳን ትምህርት ላይ አንዳች ነገር ይጨምራሉ። የሚጨምሩት ነገር ከሐሰት ትምህርት ወደ ሐሰት ትምህርት ይለያያል።

## 9. የሐሰት ትንቢት፥

ሌላው የሐሰት ትምህርቶች ጠባይ የማይፈጸመው የውሸት ትንቢቶችን መናገር ነው። የሐሰት ትምህርት መሪዎች በእግዚአብሔር የተጠራንና የተመራን ነን በማለት በድፍረት ትንቢቶችን ተናግረዋል፥ ይናገራሉም። እነዚህ ትንቢቶች ግን አልተፈጸሙም። ለምሳሌ የያህዌ ምስክሮች መሥራችና የመጀመሪያው ፕሬዚዳንት ቻርለስ ራስል የዓለም መጨረሻ እንደ አውሮጳ አቆጣጠር በ1914 ዓ.ም ይሆናል ብሎ ነበር። ነገር ግን ዓለም እግዚአብሔር በራሱ ጊዜ ፍጻሜዋን እስኪያመጣ ድረስ እስከ ዛሬ አለች /1ዮሐ. 4:1 ተመልከት።/

## የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም።

የስሕተት ትምህርቶች ዋነኛው ምክንያት የተሳሳተ የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ነው። ማንኛውም መጽሐፍ በደራሲው መንፈስና ለማስተላለፍ በፈለገው መልእክት መሠረት መተርጎም እንዳለበት ግልጽ ነው። ይህ ካልሆነ ለደራሲው ታማኝ አለመሆንና ያላለውን አለ፥ ያላሰበውን አሰበ ወደ ማለት ያደርሳል። ይህም ወደ ስሕተት ይመራል።

መጽሐፍ ቅዱስ፥ የእግዚአብሔር ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የጻፉት መጽሐፍ ነው። 2ጴጥ. 1፥21! 2ጢሞ. 3፥16-17። እንዲህ ከሆነ በዚያው መንፈስ አማካይነት ካልተተረጎመ ትርጉማችን የተሳሳተ ይሆናል።

አንድ ማስታወስ የሚገባን መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ቃል ያስተላለፈልን ሰዎችን በመጠቀም መሆኑን ነው። እንዲህ ከሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የእግዚአብሔርንም የሰውንም እጅ /ጣት/ እናያለን ማለት ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰውና ፍጹም አምላክ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስም በሰዎች እጅና ቋንቋ የተጻፈ ፍጹም የእግዚአብሔር ቃል ነው።

ከዚህ የተነግ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር ራሱን በነቢያቱና በሐዋርያቱ በኩል በተጻፈ ቃሉ ገለጠልን። እነዚህ ነቢያትና ሐዋርያት በተወሰነ ዘመንና ቦታ የነበሩ፥ የግል ስጦታ፥ ቋንቋ፥ ባህልና ታሪክ የነበራቸው ነበሩ። እግዚአብሔር በየዘመናቱ የተነሡትን የርሱን ባሪያዎች በዚህ መልክ በመጠቀም ፈቃዱን አስታወቀ፥ የብሉይ ኪዳን በዕብራይስጥ፤ ጥቂቱም በአራማይክ፥ የአዲስ ኪዳን ደግሞ በግሪክ ቋንቋ የተጻፈው መጻሕፍቱ በተጻፉበት ዘመን የነበሩ ነቢያትና ሐዋርያት ሕዝቡንም ጨምር እነዚያን ቋንቋዎች ይጠቀሙ ስለነበረ ነው።

ከዚህም ጋር ለተጻፉት መጻሕፍት ዘመን ቀረብ ብለው የነበሩ አባቶች የተጻፈውን ቃል በምን ዓይነት መንፈስ ተረዱት ወይም ተረጎሙት ብሎ መጠየቅም ይጠቅማል። ለምሳሌ ያክል ከጌታችንና ከሐዋርያት ዘመን አንሥቶ እስከ 6ኛው /ስድስተኛው/ መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ የግሪክ ቋንቋ በሜድቴራኒያን ባሕር አካባቢ በነበሩ የሮማ ግዛቶች ውስጥ የመግባቢያና የሥነ ጽሑፍ ቋንቋ ሆና ቆይቷል። በዚያን ዘመን የነበሩ ጌታን ያመኑ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ቃሉን እንዴት ተረዱ ብሎ በመጠየቅ ከእነርሱ መማር፥ በዘመናት ሁሉ ያልተገለጠ የእግዚአብሔር እውነት ለኔ ተገለጠልኝ በማለት የሐሰት /ትምህርት/ አስተማሪ ከመሆን ያድናል። ቃሉ

«የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሩአችሁን ዋናቻችሁን አስቡ፤ የኑሮአቸውንም ፍሬ እየተመለከታችሁ በእምነታቸው ምሰሉአቸው» ይላልና። ዕብ. 13፥7። ስለዚህ ጤናማ የሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ለሁላችንም አስፈላጊ ነው። የስሕተት ትምህርቶች ዋነኛው መንስኤ የተሳሳተ የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ነው።

የሚከተሉትን መመሪያዎች ጤናማ በሆነ መንገድ ቃሉን ለመረዳትና ለመተርጎም ከጥንት ቤተ ክርስቲያን ጀምሮ የእግዚአብሔር ሰዎች ሲጠቀሙ ቆይተዋል። ስለዚህ ሁላችንም በመመሪያዎቹ ብንጠቀም በማስተዋል፤ በጥበብና በትሕትና ቃሉን ለመረዳት ይጠቅመናል ብለን እናምናለን፡-

## 1. ቃሉን ግልጽ በሆነ /መሠረታዊ/ ትርጉሙ መረዳት /መተርጎም/፡-

ከላይ እንደገለጽነው የእግዚአብሔር ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው ቃሉን ሲጽፉ ቋንቋቸውን ተጠቅመዋል፡- ቋንቋ ደግሞ የሰዋስው ሕግና አገባብ አለው። ከዚህ የተነሣ አንድ ሰው የቃሉን ትርጓሜ ለማግኘት የተደበቀ ወይም የተሰወረ ነገር ከራሱ ሳይፈጥር በቀጥታ ይህ የማነበው ቃል «ምን ይላል?» ብሎ በመጠየቅ ግልጽ የሆነ ትርጓሜውን መውሰድ አለበት። የሚከተሉት ነገሮች መጽሐፍ ቅዱስን በመሠረታዊ ትርጒሙ በመረዳት ውስጥ ይጠቃለላሉ።

### ሀ. የቃሉን ወይም የአረፍተ ነገሩን የመጀመሪያ ትርጒም መገንዘብ፤

የቃላት ትርጒም አብዛኛውን ጊዜ ከዘመኑና ከአካባቢው ጋር የተገናኘ ነው። ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃል መጀመሪያ በተነገረ ወይም

በተጻፈ ጊዜ ለአድማጮቹና ለአንባቢያን ምን ትርጉም ሲሰጥ ነበረ ብሎ መጠየቅ አግባብ ያለው ነው። ስለዚህ የቃሉን ትርጉም በመረዳት ለራሳችን ያለውን መልእክት ከመውሰዳችን በፊት በተቻለን መጠን የተጻፈበትን ሁኔታና /የመጀመሪያ/ ትርጉም ማወቅ አስፈላጊ ነው።

ለ. የሥነ ጽሑፉን ዓይነት መለየት፤

መጽሐፍ ቅዱስ በተለያዩ የሥነ ጽሑፍ ዓይነቶች የተሞላ ነው። ስድ ንባብ፤ ቅኔ፤ ምሳሌዎች፤ ራእዮች፤ ታሪኮችና የመሳሰሉት ይገኙበታል። በመጽሐፍ ቅዱስ የሚገኘውን ቅኔ ወይም ራእይ አንድ የታሪክ ወይም የስድ ንባብ ክፍል እንደሚተረጎም መተርጎም አግባብ ያለው አይደለም። ከዚህም ሌላ ምሳሌያዊ አነጋገሮችንና ዘይቤዎችን ለየት ባለ መንገድ መተርጎም ያስፈልጋል።

ሐ. ቃሉን ወይም አረፍተ ነገሩን /በቅደም ተከተሉ/ በአገባቡ መሠረት መተርጎም፦

አንድ ቃል ወይም ጥቅስ ከመተርጎም በፊት የሚቀድሙትንና የሚከተሉትን ጥቅሶችና አንቀጾች ማንበብና ይዞታቸውን ማወቅ ጥቅሱን ለመተርጎም አስፈላጊ ነው። አንዳንዴም በጥቅሶችና በአንቀጾች ሳንወሰን ምዕራፎችንና መጽሐፉን በሙሉ በማንበብ መገንዘብ አስፈላጊ ነው። አንድ ጥቅስ የሚቆመው ብቻውን ሳይሆን በቅደም ተከተል ካሉ ጥቅሶች፥ አንቀጾችና ምዕራፎች ጋር በሐሳብ ተገናኝቶ ስለሆነ አገባቡን በቅርብም በስፋትም መመርመር ያስፈልጋል። እዚህ ላይ ማስታወስ የሚገባን አሁን በመጽሐፍ ቅዱሳችን የምናየው የምዕራፍና የቍጥር ክፍፍል መጀመሪያ ሲጻፍ እንዳልነበረ ነው። ብሉይ ኪዳን

በምዕራፍና በቍጥር የተከፈለው በ1445 ዓ.ም ሲሆን አዲስ ኪዳን ደግሞ የተከፈለው በ1551 ዓ.ም ነው። ስለዚህ ከጊዜ በኋላ በተደረገው በምዕራፍና በቍጥር ክፍፍል ሳንገደብ ሐሳቡን ለማግኘት የሚቀድመውንም የሚከተለውንም ማንበብ ያስፈልገናል።

## 2. መጽሐፍ ቅዱስ ራሱን ይተረጕማል:-

በመጽሐፍ ቅዱስ አንድ ጥቅስ ወይም አንድ ክፍል ትርጕሙ ግልጽ ካልሆነ ወይም ጥያቄ የሚፈጥር ከሆነ በሌሎች ግልጽ በሆኑ፥ በማያሻሙ ጥቅሶችና ክፍሎች አንጻር መተርጎም አለበት። ይህም የሚሆነው የመጽሐፍ ቅዱስ ደራሲ አንድ አምላክ በመሆኑና በውስጡም የሚገኘው መንፈስና ሐሳብ አንድ ስለሆነ ቃሉ አንድነት እንጂ እርስ በርስ የመቃረን መንፈስ ስለሌለው ነው። በዚህ ዓይነት ቃሉን መተርጎም፥ በማስተያየት የመተርጎም መንገድ ይባላል። በዚህ መልክ ሲተረጎም የሚከተሉትን ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ይጠቅማል:- 1ቆር. 2፥13።

### ሀ. በመጽሐፍ ቅዱስ ዓላማ መሠረት መተርጎም።

የመጽሐፍ ቅዱስ ዋና ዓላማ መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ወይም መልእክት ለሰዎች ማብሠር ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ዋና ዓላማ ስለክዋክብት፥ ስለ ከርሠ ምድር፥ ታሪክ፥ መልክዓ ምድርና የመሳሰሉትን ማስተማር ስላልሆነ እነዚህን ለማጥናት የሚፈልግ ሌላ መጽሐፍ መፈለግ ያስፈልገዋል። ሐዋርያው የመጽሐፍ ቅዱስን ዓላማ ሲገልጽ እንዲህ ብሎ ይጽፋል «ከሕፃንነትህ ጀምረህ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን፥ መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳን መጻሕፍትን አውቀሃል። የእግዚአብሔር ሰው

ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።» 2ጢሞ. 3፥16-17።

ይህ አተረጓጎም ለመላው መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ሳይሆን ለእያንዳንዱም ክፍል አስፈላጊ ነው። እያንዳንዱ ክፍል ለምን እንደዚያ እንደተጻፈ ዓላማውንና ሁኔታውን ማወቅ ያስፈልጋል። ለምሳሌ ያህል ሐዋርያው ያዕቆብ በመልእክቱ «እምነት ከሥራ ተለይቶ የሞተ ነው» ብሎ የጻፈው፥ እናምናለን እያሉ በግብረገባዊና ኅብረተ ሰባዊ ኑሮ በግድየለሽነት ለሚኖሩት ሲሆን፥ በአንጻሩ ደግሞ በገላትያና በሮሜ ሐዋርያው ጳውሎስ «ነገር ግን ለማይሠራ ኃጢአተኛውንም በሚያጸድቅ ለሚያምን እምነቱ ጽድቅ ሆና ይቆጠርለታል» ሲል በግብረገብ ሥራቸው ብቻ በእግዚአብሔር ዘንድ ተወዳጅነትንና ጽድቅን እናገኛለን ብለው ለተመጻደቁት ሰዎች ነበር። ሁለቱም ሐዋርያት የጻፉት ተነጣጥሎ ለየብቻ ሲታይ የሚታረን ቢመስልም የተጻፈበትን ሁኔታና የሰዎቹን ዓይነት ስናይ የሚደጋገፉ እንጂ የሚለያዩ ወይም የሚታረኑ ሆነው አናገኛቸውም።

ለ. ክፍሉን በተመሳሳይ ርእስ ላይ በሚናገሩ በሌሎች ክፍሎች አማካይነት መተርጎም።

ለምሳሌ ያክል ራእይን ስንተረጉም ሌሎች የትንቢት መጻሕፍትና ክፍሎች ስላሉ ከእነርሱ ጋር እያገናዘቡ መተርጐም አስፈላጊ ነው። ስለጥምቀት፥ ስለቅዱስ ቁርባን፥ ደኅንነት፥ ንስሐ ወዘተ... የሚናገሩትን ክፍሎች ስለእነዚህ

አርእስት ከሚናገሩ ከሌሎች ክፍሎች ጋር እያመሳከሩ መተርጐም፦ አንዱን ጥቅስ ብቻ ወስዶ ሌሎችን ተመሳሳይ ጥቅሶች ከመርሳት ያድናል።

ሐ. የቀደመውን በኋለኛውና ሙሉ በሆነው መገለጥ አማካይነት መተርጐም።

አዲስ ኪዳን ከብሉይ ኪዳን በኋላ እግዚአብሔር ፍጹምና ሙሉ በሆነው ልጁ ራሱን የገለጸበት ነው። «ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጐዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ፥ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን...» ዕብ. 1፥1-2። «ሕጉ ሊመጣ ያለው የበጎ ነገር እውነተኛ አምሳል ሳይሆን የነገር ጥላ አለውና...» ዕብ. 10፥1።

ስለዚህ ብሉይ ኪዳን የሚተረጐመው እግዚአብሔር በአዲስ ኪዳን በገለጠው ፍጹምና ሙሉ መገለጥ መሠረት ነው። እንደዚሁም ሐዋርያት በመልእክቶቻቸው የወንጌላትና የትምህርቶቻቸው ይዘት ምን እንደሆነ አብራርተው አስተምረውናል። ስለዚህ መልእክቶቻቸው ወንጌላትን የሚያብራሩልን ናቸው።

## 3. መጽሐፍ ቅዱስ ሊተረጐም የሚችለው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ብቻ ነው፥

የእግዚአብሔር ቃል በጻፈው በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ይተረጐማል። በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ምክሩንና ሐሳቡን ካልተገነዘቡ «ለፍጥረታዊ ሰው ሞኝነት» መስሎ ሊታየው ይችላል።»

በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ቃሉ መተርጐሙ በኛ በኩል ሊደረግ የሚገባው ዝግጅትና ጥናት ይቀራል ማለት አይደለም። በመንፈስ ቅዱስ በማሳበብ ቃሉን አንብበው ቅደም ተከተሉን፣ ባህሉን፣ ታሪካዊ ይዞታውን ወዘተ ተመልክተው ትክክለኛ ትርጐሙን ለመረዳት ጥረትና ዝግጅት ሳያደርጉ የመጣላቸውን የሚናገሩና የሚሰብኩ አንዳንድ ሰዎች አሉ። ይህ ግን ስሕተት ነው። ማንኛውም ምእመንና አገልጋይ በጸሎት መንፈስ በመሆን የቃሉን ትርጉም ለመረዳት ከፍተኛ ጥረትና ጥናት ማድረግ አለበት።

መንፈስ ቅዱስ በምእመናን ሁሉ ውስጥ የሚኖር የኅብረት ወይም የጋራ መንፈስ ነው። 1ቆር. 12፥12። ከዚህ የተነሣ እግዚአብሔር በቃሉ ለብቻዬ ያስተምረኛል እያልን በቤተ ክርስቲያን በኩል የሚሰጠውን ትምህርትና አገልግሎት መናቅ የተሳሳተ አካሄድ ነው። በቤተ ክርስቲያንም በእውነትና በትክክል ተጠርተው በማስተማር የሚደክሙትን አገልጋዮች አለመስማትም ትክክል አይደለም። መንፈስ ቅዱስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተለያዩ ስጦታዎችን እየሰጠ ምእመናንን በጋራ የሚያንጽ ስለሆነ እውነቱ ለኔ ብቻ ተገለጸልኝ ብለን ሳንኩራራ ከእርስ በርስ በተሰጠን ጸጋ መጠን ልንማማር ያስፈልገናል። መጽሐፍ ቅዱስን በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ለመተርጐም መቻላችን ከሌሎች መሰል ክርስቲያኖች ጋር ኅብረት እንዳይኖረን የሚያደርግ አይደለም። መንፈስ ቅዱስ የአንድነት የፍቅርና የትሕትና መንፈስ ነውና።

## 4. ቃሉ አሁን ለኔ /ለኛ/ ምን ይላል?

መንፈስ ቅዱስ ሕያው መንፈስ ስለሆነ በቃሉ አማካይነት እያንዳንዳችን አሁን ላለንበት ሁኔታ ይናገራል። ያነበብነው ቃል መጀመሪያ በተነገረበት ወይም

በተጻፈበት ጊዜ ምን ትርጉም ነበረው? በአገባቡና በሙላው መጽሐፍ መሠረት ምን ትርጉም አለው? ብለን ከጠየቅን በኋላ ዛሬስ ለእኔ /ለእኛ/ ምን ይናገራል? ለማኅበረ ምእመናናችንስ ምን መልእክት አለው ብለን መጠየቅ ይገባናል። ማንኛውም ተቀዳሚ ዝግጅት ቃሉን ለሕይወታችን ወደምንሰግበትና ወደምናዋህድበት ደረጃ እንዲያደርሰን ያስፈልጋል። ቃሉ ዛሬ ለእኛ በሚናገርበት መልእክት መሠረት ስንሄድ እግዚአብሔርን የምንከተል፥ ከስሕተት ትምህርት የተጠበቅን በብርሃን የምንጓዝ መልእክተኞች እንሆናለን።

## መደምደሚያ።

በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ማመንና ማጥመቅ የእግዚአብሔር ቃል ራሱ የሚያስተምረው ነው። የእግዚአብሔር ቃል በሦስቱ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ መካከል መተሳሰብ፥ የእርስ በርስ መከባበር እንዳለ ቢያሳይም ሦስት መለኮት እንዳላቸው አያሳይም። ነገር ግን አንድ ባሕርይ፣ አንድ ፈቃድ፣ ችሎት ወዘተ እንዳላቸው ያሳያል። ይህን ደግሞ ሲያደርግ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ መካከል ልዩነትም እንዳለ ይገልጻል። ከዚህ የተነሣ እግዚአብሔር በባሕርይ አንድ በአካል ግን ሦስት ብለን እናምናለን። ይህ ቃሉ የሚያሳየንና የሚያስተምረን ስለሆነ ለአእምርአችን እንዲመች ብለን ልንለውጠው አንችልም። የእግዚአብሔር ቃል የሚገልጽልንና የሚናገረን ሁሉ ባይገባንም እንኳ የእግዚአብሔር ቃል ነው።

የአብን የወልድንና የመንፈስ ቅዱስን ሦስትነትና አንድነት ማለት ሥላሴን የሚክዱ ሰዎች በሁለት ዓይነት ሊከፈሉ ይችላሉ። አንደኛው ወገን እውነቱን ሳያውቁና ሳይረዱ ተታልለው በክህደት ትምህርት ውስጥ የገቡ ሲሆን ሁለተኛው ወገን ግን የእግዚአብሔርን እውነት ከቃሉ እያወቁና እየተገነዘቡ በስሕተት ትምህርታቸው ለመቀጠል የሚፈልጉ ናቸው።

አንባቢ ሆይ! እነሆ ይህች መጽሐፍ እግዚአብሔር ለደራሲው በሰጠው ጸጋ መጠን በአብ፥ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ መካከለ ስላለው ግንኙነትና አንድነት ከብዙ አቅጣጫ ለመግለጽ ሞክራለች። ሳታውቅ ወይም እውነቱን ሳትረዳ ወደ ስሕተት ትምህርት ገብተህ እንደሆን ሰውን ለማስደሰት ብለህ ሳይሆን፥ ይሉኝታን ሳትፈራ ወደ እውነቱ እንድትመጣ ትጋብዛለች። ሐዋርያት ሰውን ከማስደሰትና ከመስማት እግዚአብሔርን

መስማት ቁርጥ አሳባቸው እንደሆነ ሁሉ ያንተም ሐሳብ እንዲሁ ይሁን። እነዚህ የስሕተት አስተማሪዎች ሰዎችን ሁሉ የሚያድነውን የክርስቶስን ጸጋና ባለጠግነቱን ማብሠር ሲገባቸው፥ ለሰዎች ያሳየው ፍቅርና መሥዋዕትነት አልበቃ ብሏቸው ጨርሰው አምላክነቱን ይክዳሉ። አለዚያም በምሕረቱና በጸጋው ላይ ተጨማሪ የመዳን መንገድ ያለ ይመስል፦ ያ ስም ቀርቶሃል! ይህ ፎርሙላ ይጐድልሃል! እያሉ ያልጸኑትን ነፍሳት ያታልላሉ።

ወንድሜ ሆይ! እምነትህ በአንዱ አምላክ፥ በአንዱ እግዚአብሔር ይሁን። ይህም አንዱ አምላክ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ በሦስትነት እንደተገለጸ እወቅ። የመዳንህ ትምክህት በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመንህ ይሁን እንጂ ከሌሎች የተለየ እውቀትና መገለጥ አገኘቼአለሁ በሚል አይሁን። በክርስትና ደኅንነት ስጦታ እንጂ በውድድር ወይም በእውቀትና በመገለጥ ብልጫ አይደለም። «ከእውቀት ከፍለን እናውቃለንና» 1ቆር. 13፥9። «ማንም አንዳች የሚያውቅ ቢመስለው ሊያውቅ እንደሚገባው ገና አላወቀም! ማንም ግን እግዚአብሔርን ቢወድ እርሱ በእርሱ ዘንድ የታወቀ ነው» 1ቆር. 8፥2-3። ወደ እውነቱ ሁሉ የሚመራ የእውነት መንፈስ ሁላችንንም በእውነቱ ይምራን፦

አስጀምሮ ላስጨረሰኝ አምላክ ምስጋና ይድረሰው።

አሜን።

# ከተጠቀምኳቸው መጻሕፍት ውስጥ የሚከተሉት ይገኛሉ


1. "United Pentecostal Church "&" Oneness Pentecostalism" in Burgess and McGee, ed. Dictionary of Pentecostal And Charismatic Movements. Grand Rapid, MI. Zondervan, 1988.
2. Douglas, J.D ed. Dictionary of the Christian Church. Paternoster Press, 1974.
3. HoeKema, A.A. Jehovah's Witnesses, The Paternoster Press, 1973.
4. Mather, George A Dictinoary of Cults, Sects, Religions and the Occult. Grand Rapids, MI, Zondervan, 1993.
5. McDowell Josh and Stewart Don: Concise Guide To Today's Religions. Scripture Press, 1983.
6. Richardson, Alan. Creeds in the Making. Philadelphia, Fortress press, 1981.
7. ተክለ ማርያም ገዛኸኝ። እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል። አዲስ አበባ፥ ንግድ ማተሚያ ቤት፥ 1967 ዓ.ም።
8. ተክለ ማርያም ገዛኸኝ። ኢየሱስን ማን ይሉታል? አዲስ አበባ /ያልታተመ/ 1978 ዓ.ም።

9. Walker, Williston. A History of the Christian Church. New York, Charles Scribner's Sons, 1970.

10. Whitaker, E.C. Document of The Baptismal Liturgy. SPCK, 1970.

11. Bibles:- The Jerusalem Bible (JB) London Darton, Longman & Todd: 1968.

The New English Bible (NEB) Oxford University, 1970.

Good News Bible (GNB) The Bible Societies, 1976.

The Revised Standard Version (RSV) Holman Bible Publishers, 1982.

The New International Version (NIV) Zondervan, 1985

The Greek New Testament United Bible Societies, 1983.

12. መጽሐፍ ቅዱስ (አማርኛ) - የ1947 ዓ.ም. እትም።

13. መጽሐፍ ቅዱስ (አማርኛ) የ1980 ዓ.ም. እትም።

በምሁራዊ ጥናት ላይ ተመሥርቶ ዘርዘር ባለ መንገድ የተጻፈ በመሆኑ ምሳሌን በሚመለከት የተሟላ እውቀት ለሌለው አንባቢም ሆነ የመናፍቃንን ትምህርት ተቋቁሞ ለመመለስ ለሚፈልግ ለማንኛውም ሰው የሚሰጠው ጥቅም ከፍተኛ ነው የሚል እምነት አለኝ። ደራሲው ይህንን መጽሐፍ በማዘጋጀት ያሳለፉት ጊዜ በከፍተኛ ቁም ነገር ላይ የዋለ መሆኑን አንባቢ በቀላሉ ይረዳል።

ደረሰ ብሩ።

ይህ ትምህርት በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሠረተ ትምህርት ነው። ስለ ምሳሌ የተሰጡት ግብራሪያዎች በብዙ የአዲስ ኪዳን ክፍሎች የተደገፉ በመሆናቸው ለአንባቢው ጠንካራ ግንዛቤ ይሰጡታል። በግልም ሆነ በሕብረት በጥንቃቄ እንዲጠና እመክራለሁ።

ዶ/ር ብርሃኑ ሀብቴ።

ብዙ ሰዎች እውነትን እንዳለ ለመረዳት ከመናፈቅ፣ ከመጣር ይልቅ ከአእምሮ አቅማቸው ከልል ውስጥ አስገብቶ በቀላሉ መረዳትን ለማግኘት ሲሉ ብቻ እውነታን ይቀናንሳሉ ያወላክፉሉ። ከአእምሮ መካለያ የሚያልፈውን የፈጣሪን ማንነት በተፈጣሪው አእምሮ የመረዳት ወሰን ወይም አቅም ሥር ለማዋል መሞከርም ፈጣሪን ከፍጡሩ ማስተካከል ወይም ማሳነስ ይሆናል። በዚህ አኳያ ለአእምሮ እንዲመች ለማድረግ ሲባል ምሥጢረ ሥላሴን መሸሸና መሳት በጥንቃቄ የሚጠቀስ ነው።

ቄስ ዶ/ር እሸቱ በዚህች አጭር ጽሑፋቸው ያቀረቡልን ትምህርት እጅግ ጠቃሚ ነው። በጥሞና በእርጋታ ልናስተውለውና ልንጠቀምበት፣ የምንችል እያንዳንዳችን ሊኖረን የሚገባ መጽሐፍ ነው።

ሰሎሞን ከበደ።